

ሀሁ ወይም ፕፑ

አበባ ወይ እሳት

ሀሁ ሰሳም ጥሪ!

ከጸጋዩ ገብረ መድኅን



ሀሁ ጤና ዓደም!

ከሀሁ በስድስት ወር የቀጠለ ዲሞክራሲ ፈለግ ሀሁ
(የካቲት 5 1 [illegible] ዓም ተጻፈ
አዲስ አበባ)
ቅኔ ድራማ። ሥነ ግጥም ፪። ከእሳት ወይ አበባ የቀጠለ።
ተዋንያን

1. ታጋይ ነጋ ከሀሁ በስድስት ወር የሰመ ንጉሥ ጣሴ ልጅ።
17 ዓመት ተመንፈቅ።

2. ቢአራጋው። ከሀሁ በስድስት ወር የጥዱ ናደው ጡት ልጅ።
17 ዓመት ተመንፈቅ። የፖለቲካ ደሰሳ።

3. ሠለስቱ ደንኪረኞች፣ አሚናዎች፣ ዘፋኞች፣ ሼክስ[illegible]ዊ
የማክቤዝ ጠንቋዮችና ሟርተኞች።
እትማማኞች ተጋደኞች መዚቀኞች፣
ደንኪረኛ ግደይ፣ ደራኪረኛ ሌንሣና ደንኪረኛ ፉፉ።



ቢ. አራጋው ። ከሀሁ በስድስት ወር የጥሩ ናደው
ጡት ልጅ ። 17 ዓመት ተመንፈቅ የፖለቲካ
ደላላ።



ታጋይ ነጋ ተራማጅ ሀውልት ላይ ለመታሰቢያ እንደተቸነከረ

ሀሁ ወይም ፕፑ!

የአዲስ አበባ መድረክ ጥበብ ምታተኞች ሀሁ ወይም ፕፑን አዩ። አብዛኛዎቹ አነቱ። ተመልካቹም ሕዝብ ጭምር አነባ። የሀቅ ረሀብ፣ የሠላም ረሀብ የፈነቀለው የምሥራች እንባ ነው። እኛም አሰየው፣ ሁላችንንም እንኳን ለዚህ አደረሰን አልን! የኢትዮጵያ ክብርና ባህል ገሬም እንደ ልማዱ በግላጭ ተሳለቀ።

በሊላ መልኩ፣ እጅግ መራር ከሆነ የሥውር ይፋ ቢሮክራሲ ትግል በኋላ ደም፣ በቴአትሩ መክፈቻ ዋዜማ፣/ ያልጠበቅነው ነገር ባይሆንም/፣ ከፍተኛ የመሰናክል ደባ በውጪና በውስጥ ይጧጧፍ ጀመር። ቅዳሜ ነሐሴ 22 ጧት አዘጋጅ ዓለሙ ገብረአብ መድረክ መግቢያ ደረጃ ጀርባ ጥግ ሥር ተኮራምቶ፣ ሽምቅቅ ብሎ አነባ። የሰቀቀን እንባ ነው። እኛም አዩ የኛው የተለምዶ ጉድ አልን! የኢትዮጵያ ክብር ባህል ገሬም እንደልማዱ በግልባጭ ተሳለቀ።

"ዓለም የቴአትር መድረክ ነው" አለ አያልቅበት ሼክስፒር። የምሥራች እንባና የሰቀቀን እንባ መፈራረቂያ መድረክ። "ታሪክ ራሱን ይደግማል" የሚሉ አባባል ደሞ እጅግ መራር ሐቅ ነው። እልፍ ሳንል እዚያው ዞረን እንደገና ድፍን። በሕዝቦች መሀል የደም በቀል ጭር፣ ሥልጣን እናት ላይ ተጉዝር፣ ያን የማዉራረሱን ተለምዶ ጉዞ በሥነ-ልቦና ጦር እንደገና ማካረር ጠናብን ደሞ?

ጥላቻ በነገሠበት ምድር ፍቅርን በብዕር ማስፈን፣ የነፑሽኪንም አቤቱታ ነበረ። ሀሁ ሰላም ጥሪም፣ ሀሁ ጤና አዳምም፣ ዲሞክራሲያዊ ሀሁም፣ ሀሁ ፖለቲካ ድራማም፣ አበባ ወይ አሳትም፣ ይኸው ነው አቤቱታው።

አ.ገ.መ

ገቢር አንድ
ትዕይንት አንድ
ፊደል ዳንኪራ

ነጋ፡-

-/ተረት ለምስቱ ዳንኪረኞች። በነጥብ በምራት ታቅፈዋል። ሌባ ሻይ ነጋ ሽንጡን በገመድ ታሥሯል።/-

ወሀኒ ነው እንጂ መድረክማ ላይ ያባቴ ሀሁ ከተዉለመ ቆየ። ዓሥራ ስምንት ዓመቱ። በእቅድ ነው እንጂ ታድያን ባጋጣሚም አይደለ። ፊደል ገበታ የሰላም ሀሁ በድፍን አገር ስለተወገዘ ነው በየመድረኩ የተዉለመው።

ታድያን ያኔ በሰንሰለት ታሥሬ፣ በልጅነቴ በአሥር ዓመት ዕድሜዬ ይሽን ያባቴን ፊደል ወሀኒ ቤት አገኘሁት። ፊደል ገበታ ሀሁ እንደሰው ተቆራምዶ፣ ተዉራምቶ፣ ወጣት ጐልቆመሣፍርት እንደ ጉሽ ፍል እንደ ፍልሰት አነባበሮ እታመቀበት እተረመረመበት ወሀኒ ጉድጓድ ውስጥ፣ በልጅነቴ በአሥር ዓመት ዕድሜዬ ያባቴን ሀሁ ውስጣቸው አገኘሁት። እንጂ ከዚያማ በፊት ፊደል ገበታ፣ በአገር አደባባይ ላይ ከተዉለመ ቆየ።

አንዲት ቀን ብቻ አባቴ ሰሙ ንጉሥ፣ የእግዜር አጋጣሚ አግኝቶ፣ ፊደሉን ይዞ፣ እስቲ የሌባ ሻይ ባህርይ ልዋነይ ብሎ፣ ጉባዔ እሚሉት መሀል፣ ባቋራጭ ከተፍ አለ! እንዲህ እንደኔ ሽንጡን በገመድ ተይዞ ነበር፣ ሌባ ሻዩ አባቴ፣ የሞያ ጓደኛውን ያበራ ጆሮን የዕድሜ እጣ ክፍል፣ ላንዲት ቀን ብቻ ጉባዔ እሚሉት መሀል የተዋነየው። እንዲህ እንደኔ። ሌባ ሻይ ምሱን እፀፋርስ ተግቶ ሽንጡን በገመድ ታሥሮ የተዋናዮች ጀግናው አባቴ ገባ ጉባዔ እሚሉት መሀል ክንፍና ጥፍሩን አንደገሥር አናፍር።.....ተንደረደረ። ከመድረክ ማዶ ዘሎ ጉባዔ እሚሉት መሀል ዋኘ። ተዋነየ። ግን፣ ግን፣ ወዲያውኑ "እግዚኦ የሌባው ብዛት!" አለና ጮኸ! "ፈራሁ" አለ! "እግዚኦ ጉባዔ ሙሉ ሌባውን ፈራሁ አውጡኝ ባካችሁ የት አባቴ ልደበቅ!" አለና ሮጠ ተዋናይቱ ቀሚስ ሥር ተወሸቀ። ፈራ! በሌባው ብዛት ተንቀጠቀጠ። ተርበተበተ። /ቅዛዜ ልሣን/ በመጪረሻ፣ በትርኢቱ መዝጊያ፣ ነጅ ከነሳ በኋላ፣ ተዋናዩ አባቴ በመሪር ተገሰፀ። በጉዳዬው በላዮች ቀዛዛ ዛቻ አዘል ምላስ ሕዋሱን ተነደፈ። "በዙት በኩል ዞርክና ደሞ፣ ያን ሀሁ ፊደልህን፣ ዳግመኛ ደገምክብን?! ደርሰንብሀል! አውቀንብሀል! ብትጠነቀቅ ይሻላል!" ተባለ። ሕዋሱን ተቀዘዘ! ፊደሉን እንደያዘ መንፈሱን ተገረፈ። አባቴ ሰሙ-ንጉሥ።

ከዚያች ቀን ወዲህ ካባቴ ሀሁ ጋራ፣ ወሀኒ ነው እንጂ ከቶም መድረክ ላይ አልተያየንም። ገና በአሥር ዓመቴ፣ ወጣት መቀመቅ ወሀኒ መካከል። ቆሽት አንጀታቸው መሀል እምብርታቸው መካከል። ፊደል ገበታ ሀሁ እንደሰው ተቆራምዶ፣ ተዉራምቶ፣ ወጣት ጐልቆመሣፍረት እንደጉሽፍል እንደፍልሰት አነባበሮ እታመቀበት እተረመረመበት ወሀኒ ጉድጓድ ውስጥ፣ በልጅነቴ በአሥር ዓመት ዕድሜዬ ያባቴን ሀሁ ውስጣቸው አገኘሁት። ቆሽት አንጀታቸው መሀል እምብርታቸው መካከል። ታቅፈውት አየሁት ያባቴን ሀሁ።....

ከተቆራመደበት ከተዉራመተበት እኩለ ለሊት የወሀኒ ፅልመት ከመቀመቅ ዉለማ መሀል፣ እንደለሊት ትል ቃንቄ ከወጣቶቹ ቆሽት አንጀት ጥልቀት፣ ብልጭ ሲል አየሁት። ወሀኒ ዘበኞቹ ላይሰሙ ወጣቶች አሥረኛቹቹ ከቆሽት አንጀታቸው ውስጥ፣ ከተዉለመበት ጉድጓድ ውስጥ፣ ወሎ ቦረና እንደተረፈረፉት ያባቴ ተማሪዎች፣ -በዉለማ ሀ ሲሉት፣ በዉለማ ሁ ሲሉት፣ ዉርማታው ፊደል በቀስታ ሲፈካ አየሁት። ሰማሁት። ምን ይሆናል ግን አድፍጠው የነበሩት የወሀኒ ቤት ዘበኞች ወዲያው በከመቅፅበት፣ በሩን በርግደው መሣሪያ አቀባብለው በወጣቱ ላይ ተጋረጡበት። ያንን ዉርማታ ያባቴን ፊደል ከአቅፋቸው መካከል በጠመንጃ ነጠቁት። ሁለተኛ አንድም ወጣት አሥረኛ፣ እንኳን በብርሃን በእኩለ ለሊት ወሀኒ መቀመቅ ፅልመት ውስጥም ተቀበሮ፣ ሀሁን እንዳይቆጥሩበት፣ ሀ እንዳይሉበት ሁ እንዳይሉበት፣ እስከ ወዲያኛው ለመቀጣጫ ብለው፣ ዓይናቹ አያዩ ያባቴን ፊደል ከወጣቶቹ ቆሽት አንጀት መሀል በጭቀው ነጥቀው፣ በረጅም ገመድ ሽቅብ ጣራው ጫፍ አናት፣ እንደሰው ልጅ ሰቀሉት። ፊደሉን። እንደሰው ልጅ አንጠለጠሉት። ለካስ ፊደልም እንደሰው ይቀሰቀላል። ወሀኒ ጣራ ላይ ይንጠለጠላል። በእኩለ ሌሊት። ዉለማ በነገሠበት ጊዜ።

እንጂ ያኔ ታሥሬ በአሥር ዓመቴ በልጅነቴ ዕድሜዬ፣ ያባቴን ፊደል ወሀኒ ዉለማ አየሁት እንጂ ሕዝብ መድረክ ላይ የሰላም ሀሁ ከተዉለመ ከተረመረመማ ቆየ።

-/ መድረክ መብራት ይፈካል። ሀሁ ወይም ፐፑ አቨርቸር እየመጠቀ ነጋና ዳንኪረኞቹ፣ ፊደል ዳንኪራ ይደነክራሉ። ግዕዝኛ፣ አረብኛ፣ ላቲንኛ ይይዛሉ። /-

አቨርቸር፡- ሀሁሂሃሄህሆ
ወይስ ጦር ፐፑፓፖ!
አቡጊዳ ቀይሶ
ወይም ሰላም ፈልሶ
ሚሊዮን ሰው ገንዞ!?
መልእክተ ላብ አደር
ወይም የአሥራ ሰባት ጠር!
ሰላም ሀሁሂሃሆ
ወይስ ጦር ፐፑፓፖ!

:-/ መብራት ይጨልማል። እሩምታ ይተኩሳል። ኡኡታ ይቀልጣል። ዋይታ ይቀልጣል። መብራት ይበራል። ነጋ እንደታጠቀ ከሕዝብ መሀል ተንደርድሮ ተኩሰና ኡኡታ ወደ ተሰማበት መድረክ መሀል ይቆማል።/-

ነጋ፡-

ጣርና ጦር! ለሰላም ቆምን ብለን በተማማልን ማግሥት፣ ዲሞክራሲያችን ጣር ሰላማችን ጦር ይሆናል።

ይኸው! ጣርና ጦር! ያባት ውርስ ነው። ያባቶች እርግማን ነው። ሰላምና ዲሞክራሲ እኮ አይታቀብልንም።

መርገምት አለ ደግችን ውስጥ
መመርመር አለብን በግልጥ!
ኢትዮጵያዊ እምንባል ዘር
ሳንተላለት ባሰቸኳይ፣ ተይዘን ቶሎ እንመርመር!
ከሶማሊያም ከዩጉዝላቪያም
ይብሳል የኛው አሊዳም!....
እንመርመር።
መቅሰፍት አለ ደግችን ውስጥ
ቃል የሚያስከድ ልማነ-ብልጥ
መሀላ የሚያስገለብጥ
ሽምጥጥ የሚያስደርግ ባንዲ
የደም ጦስ የሥልጣን ውርዴ
የእጥንት እከክ
ሰግብግብ ሰንክ
አለብን ከደሊ መከር
አበሻ በምንባል ዘር
ከውልደት የተበከለ
የጥቁር ፋሺስትነት ውርስ፣ በደግችን መቅሰፍት አለ።....
እንመርመር።

-/ ረዥም ፋታ። ዳንኪራ ቡድን እንመርመር ዳንኪራ በቢ.አራጋው መሪነትና ግንባር ቀደም ቀግራት እየደነከረ ይገባል። ዳንኪራው ወሎዬ ግጋናግ አሊ ዘፈን ላይ ይመሠረታል/-

እንመርመር ዳንኪራ: እንመርመር።
ሰላምና ዲሞክራሲን እፋኝ ነገር
በደግችን የሠረፀን ክፉ መከር
እንመርመር።

-/ በብራት በፍጥነት ይጨልግል። ትእይንት አዳም አንድ-ይቀጥላል/-

አቋም አንድ

–/ነጥብ መብራት በተቆላለፉ ክንዶች ላይ ይበራል። ክናዶቹ የነጋና የቢ.አራጋው ናቸው። የአረሆዎች ጥሪ ዜማ በጪለማ በሕብር ያስተጋባል። አጭር ፀጥታ/–

ነጋ :ተሣሥረናል። ክናዶቻችን ተቆላልፈዋል።
ቢ.አራጋው:አንድ ነበርን። የአንድ እናት ልጆች ነበርን።
ነጋ :የአንድ እናት ልጆች ነን። ....አንተ ግን ተሸምከክ። ተሸለምከክ። ናጠጥክ። አድር ባይ ነህ።
ቢ.አራጋው:አንተ ግን ተሰደድክ። ታጠቅክ። ታጋይ የምትባል ነህ።
ነጋ :አንተ የከተማ ደላላ ሆነህ ቀረህ።
ቢ.አራጋው:አንተ የበረሃ ጊንጥ ነህ።
ነጋ :አቋማችን እየቅል ነው።
ቢ.አራጋው:ዕድላችን ተከፋፈለ
–/የተቆላለፉት ክንዶች ይለያያሉ/–
ነጋ :ገና አቋም ለአቋም፤ ዓላማ ለዓላማ፤ ክልል ለክልል፤ ቋንቋ ለቋንቋ እንፈላለግለን።
ቢ.አራጋው:ገና እንተያያለን።
ነጋ :ግን እንደተለያየን ከቶም አንቀርም።
ቢ.አራጋው:እሱን እኔ እንኛ።
–/ነጥብ መብራት ይጠፋል። ዳንኪራ ቡድን አረሆ ዜማ ያስተጋባል።/
/አረሆዎች/–አሥራ ሰባት ዓመት በደገሠው ሠርግ
ጓድ ኢሠፓ ደርግ
አማከሎ ገባበት ወያኔ ኢህአዴግ።

ትእይንት ኪራይ ቤት ይቀጥላል።



ሎሬት ፀጋዬ ከተሞንያኑና ከመድረክ ሞያተኞች ጋር

ሰው።
-/ወደ ቢ.አራጋው ዞሮ በበለጠ ቀዛዝ አንደበት/-
አየሀ፣
ወንድሜ ቢያንካ አራጋው፤
አንተ። አየሀ፤
አንተ የዚህ ብጤው ሰው ነህ።
ቃል-የለህም።
ዓላማ-ቢስ ገለባ ነህ።...
አየሀ!
-/ፋታ። ያዘላትን ሕፃን አልጋው ላይ ያጋድማታል።/-

ቢ.አራጋው: -/በአጋኖ/
ካደኛ!? ይኼንንም ካጀኛ! የቤቴን ሳሎን ቀን ቀን ለዳንኪረኛ፣ ማታ ለማታ ክቡብ ሞያ ጭፈራ መለማመጃ መድረክ፣ ግን ከአንድ ሰዓት ጀምሮ፣ ለኔ ብጤ ከርታታ ሶማሌ ዘመድ ማከራየቴን፣ ቀን ለዳንኪረኛ ማታ ለስደተኛ ማከራየቴን፣ አልነገርከኝም በለኛ?! ካ ደኛ?!... ያውም ከነምልክቱ፤ ያውም ከነምልክቱ፣ ቀን ለዳንኪረኛ መለማመጃ፣ ማታ ለስደተኛ መኝታ ሥፍራ አከራየሁ ያልኩህ ቀን፣ ዳንኪረኞቹን ራሴ በልዩ ፈጠራዬ እኔ ቢ.አራጋው አዘጋጅቼ፣ አዘጋጅና ኮሪኦግራፊስት ሆኜ እንዳስለጥናቸው ተፈራረምኩ ስልህ፣ እኔም አንድ ነገር ትዝ አለኝ፣ ልነግርህ የፈለኩት እኔም አንድ ነገር ትዝ አለኝ አዘጋጅ ቢ.አራጋው አላልከኝም ነበረ!? ከነምልክቱ!...

እንዳባቴ እንደሰሙ ንጉሥ እኔም በልጅነቴ፣ እዚያው ወሎ ገራዶ፣ በደሴ ዙሪያ ጀርባ ኡርጌሳ ምድር፣ ተወልጄ ባደግኩበት የመንደሬን ልጅ እያሰባሰብኩ ሀ ሳሰኝ ሁ ሳሰኝ፣ አበገዳ-አበቸደ ሳስቆጥር፣ ስጮህ ሳንቋርር፣ ትንሽ ተዋናይነት ልክፍት ተለከፍኩ አላልከኝም?! በል?! እንደባለኩራዙ ከርታታ አባቴ፣ ፊደል ገበታ ለፋፊ ሂዳተኛ፣ እያስቆጠርኩ እያስለፈፍኩ ተዋናይነት በልጅነቴ ተለከፍኩ አላልከኝም?!...

ይኸውና ሞክረዋ! ሜዳውም ይኸው ፈረሱም ይኸው! ዘንድሮ እንደሆነ ሁሉም ቴአትረኛ ነው! አንተስ ለምን ይቅርብህ?! እኮ ና በላ!

ቢ.አራጋው: /ቢ.አራጋው ነጋን ወደ መድረክ እየጋበዘው፣ ተፍ ብሎ መድረክ መሐል ፊት ለፊት ተዝናንቶ።/- በላ!

ነጋ : /በቅዛዜ/ ምን ልበል?

ቢ.አራጋው: አላጠናህም እንዴ?

ነጋ : ምን?

ቢ.አራጋው: ስላስነበብኩህ ባህርይ፤ ስለተዋናዩ ሰው የዕድሜ ዕጣ ክፍል!?

ነጋ : ዕጣ?

ቢ.አራጋው: የተዋናዩ።

ነጋ : ክፍል?

ቢ.አራጋው: የዕድሜ ዕጣ ክፍል። የተዋናዩ።

ነጋ : /ረዥም ፋታ።/ ወረቀቱ ጠፋብኝ። ሌሊት ፀጥታ ጥበቃ ሥራ ጊዜ፣ ወረቀቴ ጠፋብኝ። -አባቴ ሰሙ ንጉሥ ያወረሰኝ ወረቀት፤ መድረክ ሥራ ዝግጅት መመሪያ ጥናት ጭምር፣ ወረቀቴ ጠፋብኝ። -/ፋታ/- ድንገት እንደአቴት ከጀ ጠፋና እራቁቴን አስቀረኝ። -/ፋታ/- ይሁንና ያልከኝን ባህርይ አሁንም ቢሆን እሠራዋለሁ።እዋነየዋለሁ።...ሳልዋነየው አልሞትም!! /ሊዋነይ እንደመቃጣት ቀኝ እጁን ፎርማላዊ ይዘረጋል።/

ቢ.አራጋው: ሳታጠና?! ሳትለማመድ?! ይኸማ እንደአደባባይ ሸቃይ ቴራቲረኛ፣ ሳያጠና ሳይለማመድ ቲኬት ቡጨቃ ብቻ ሕዝብ እናት ላይ በድፍረት ፊጥ እንደሚሉት ሆንክ ማለት ነው!..... ሳታጠና? በለብለብ? ሳትለማመድ?

ነጋ : በል ታድያ አስጠናኛ። አለማምደኛ።

ትዕይንት ሁለት

ኪራይ ቤት

ቢ.አራጋው: /ስልክ ይዟል።/ –አፍ እምተረፈ ልብ ይነብብ እኮ ነው!.....

ከልብ የተረፈን አፍ ያነበንባል!...አልኩት። አልኩት። አልሰማህም አለኝ እንጂ– አውቆ ለግሞ ልቡን ሎጉሞ – አልሰማህ አለኝ እንጂ ደጋግሜ ነገርኩት።... እኔን አይተህ ተቀጣ አለ ወንድም ሶማሌ!... የቤቴን ሳሎን፣ የገዛ እናቴን የእመት ጌኔ አምበርብር ቤቴን፣ ለስደተኛ ሶማሌ ወንድም ላከራይበት፣ አንተ ውጣልኝ አልኩት። አንተ ወንድም ባትሆነኝ ወንድም የሚሆነኝ ሰው፣ የኔ ብጤ ከርታታ ወንድም አገኘሁ ላከራይበት አልኩት።...ያውም በዶላር! የምሥራች! ጣቢያህ እዚህ ድረስ ነው ታጋዩ ነጋ ና ውረድ በቃኝ፣ ውጣ ከቤቴ፣ አለበነዚያ በግረጋጊያ ጠመንጃ ትጥቄ አሳይሀለሁ አልኩት።... አዎን ብያለሁ። አዎን ይመዘገብ። እኔ ቢ. ቢያንካ አራጋው አረጋጋው በገዛ ቃሌ፣ በገዛ መብቴ፣ በገዛ ቤቴ ምን ያደባብቀኛል። አልጨነቅም በቃ። መጨነቅ ቀረ እንደተባለ አታውቅም? !...አቤት? ሀሎ? አቤት?.... ክስህ ውሳኔ አግኝቷል?! ተፈርዶልሃል?! አትለኝም!... አትለኝም! ... /መሬት ይስማል/... ሀሎ! የቤቱ ካርታ፣ ባንተ ስም በውርስ የተመዘገበ ነውና፣ ነጋ ወንድምነቱን ማረጋገጫ አንዳችም ሰነድ ሊያቀርብ ስላልቻለ፣ ያለፍቃድህ ሊዳብልህ አይችልም፣ ተብሎልሃል አልከኝ?!... በል እስቲ አሁንም ደጋግመህ በለኝ በወለደች እናትህ! በሐቀኛ ፍርድ አምላክ ቀበሌ–ጓዴ ይሽንን የምሥራች፣ ባክህ ደጋግመህ በለኝ! –/መሬት ይስማል/ ይኼ ነኝ እኔ እኒህ የበላይ–ታጋይ ሰዎች፣ አንዳንድ ጊዜ የፍርድ ችሎታቸው እንጀት ያርሣል ብዬ ነግሬህ የለ?!.../ነጋ ይገባል። ቢ.አራጋው ስልኩን ይዘጋል።/

የቀበሌዋን ዳንኪረኛ ጉረቤት እንኳ ከጓደኞችዋ ጭምር ብቸኝነት እንዳይሰማህ አላስተዋወኩህም?! አላጨባበጥኩህም? ከበረህ ስትመጣ አድባሬ ብዬ ቤታችንን አንጥፌ ጉዝጉዜ ተቀበልኩህ። –ክፉ ነገር አላረኩህ። አልበደልኩህ። አድባሬ ነህ አልኩህ። አገሬ አንተ ነህ አልኩህ። ሥጋዬ የሥጋዬ ቁራሽ፣ አጥንቴ ያጥንቴ ፍላጭ፣ ደሜ የወንድሜ የሰሙ ንጉሥ ጣሴ የከርታታው የወሎ ቦረን መምህር የኔው ነህ አልኩህ።

–በል እስቲ አንተው ፍረደኝ። –አንበሳ አክለህ ድንገት ከተፍ ያልክለት፣ እኔ ዘመድህ የሥጋህ ቁራጭ፣ ቁጤማ አላስጐዘጐዝኩልህም? በል! ሰሌን አላስነጠፍኩልህም? በወሎ ቦረን በእናትህ ሥርዓት ጀበና አላፈላሁልህም? አድባሬ አንተ ነህ፣ መሬቴ አንተ ነህ፣ ቀዬዬ አንተ ነህ ብዬ፣ እኔው ራሴ ምድር ተንጥፌ አልተቀበልኩህም ወይ!? ወንድ፣ የጀግኖች ጀግና ዘመድ፣ እንደመለኮት ከሰማይ ዱቦ አለልኝ፣ ጉረቤቶቼ አልል በሉልኝ፣ የቀበሌ አውጋር ተቀበይልኝ፣ ብዬ ሁሉን ጠርቼ በታላቅ ክብር አላስቀበልኩህም ወይ! በል እስቲ አንተው ፍረደኝ?!

.....ታድያን ዛሬ ሶማሌ ዘመድ፣ የቤቴን ሣሎን በዶላር የሚከራይ፣ አምላክቀ ከሰማይ እንደ ሕብስተ መና ዱብ ባያደርግልኝ እጄ ላይ፣ እንዴት ትመቀኝኛለህ እባክህ፣ የወንድሜ ልጅ ታጋይ ሰሙ ንጉሥ ጣሴ ሆይ?!....ሆሆይ!!....–/በከፍተኛ ምሬት / –አፍ እምተረፈ ልብ ይነብብ እኮ ነው!... ሆሆይ!!ሆሆሆይ!!

–/ዳንኪራ ቡድን ሆሆይ እያለ ሙሾ ይደረድራል። እየደነከረ ይወጣል። ዳንኪረኛ ግደይ ወደ ኋላ ቀርታ ነጋን ትጨብጠዋለች።/

ቢ.አራጋው: /በአጋኖ/– አስተዋውቄህ የለ? ! አጨባብጨህ የለ?! – /ግደይ በሀፍረት እጇን ነጥቃ በፍጥነት ትወጣለች/–

ነጋ : –/ እጅግ በቀዘዘ ልሣን መድረክ ግንባር ወደ ሕዝቡ/

ቃል የለውም።
ሰው ልሣኑ ቃል–አልባ ነው።
ሰው።
ያለ ዓላማ።
ቢያማ፤
ቢያቅማማ፤
ቤትነከነከ በአንደበቱ
ቃል–የለውም።
ቃል አልባ ነው።

ቢ.አራጋው: ሕዝብ ፊት? ሕዝብ ላይ መለማመድ የተዋናይ ጥበብም አይደል። ድፍረት ነው። አይደረግም ይልቅ ወደ መድረኩ ጀርባ መለማመጃ ክፍል ፈልገን፣ እንደገና ሀ ብለን እንደገና ሁ ብለን እንደፈደል ጀምረን፣ በሥን-ጥበብ እውነት ክብርና ደንብ፣ የተዋናዩን ዕድሜ እጣ ክፍል፣ ለሕዝብ ሰላም መስዋዕትነት ቁመን እንለማመድ። ና!!

ነጋ : እኔ ነኝ ወዳንተ እምመጣ፣ አንተ ነህ ወደኔ እምትመጣ? ወገናኛችን የት ላይ ነው?/ነጋ በፍቅም ቁጣ ይጋፈጠዋል። ቢ.አራጋው የሞት ቅርበት ድንገት በደመ-ነፍስ በትፅበት አስደንግጦት ገሸሽ ሲል መብራት በፍጥነት ይጨልግል። ዳንኪራ ቡድን እንደማከቤዝ ሠለሥቱ ጠንቋዮች ከጨለማ ውስጥ እያንቋረሩ ይገባሉ።/

ፉፉ : -/በጨለማ/-የት ይሆን የምንገናኝ!! መች ይሆን የምንገናኝ!!

ሌንጣ : -/በጨለማ/-ሦሥታችን የምንገናኝ!!

ግደይ : -/በጨለማ/-ልጣናችን እሚቀናጅ!!

/ሦሥቱ/ : -/በጨለማ/-መቼ!!?

-/የደበዘዘ መብራት በዝግታ ብልጭ ይላል። መድረኩ በጠለ ታጥኗል። ነጉድጓድና መብረቅ ሲያስተጋባ ሠለስቱ የቃልቾች ርኩስ መናፍስት ይሰግሉ።/-

ፉፉ : -መች ይሆን ምንገናኝ?
ሰላታችን የምንገናኝ?
የዝናብ ቸነፈር ወርዶ፣ ወጪው ብርሃንን ሲገሥ?
ቅዝቃዜ ባየር ሲነግስ?
ሰማይ በመብረቅ ሲታረስ?
ነጉድጓዱ ምድርን ሲያፈርስ?
መች ይሆን የምንገናኝ?

ሌንጣ : ጀግና ለጀግና ሲዋቃ፣
መስክ በደም ተጥለቅልቃ፣
የምሱን ተፍቶ ሲያበቃ፣
ጥምብ አንሳ ባስከረን ሲዋኝ፣
ኮከብ ቆጥረን እንገናኝ።

ግደይ : ያማ ጀምበር ስትጠልቅ ነው።

ፉፉ : ሥፍራውን የት ላይ እናርገው?

ሌንጣ : ቁጥቋጦው ነው የሚሻለው።

ግደይ : ታጋይ እዚያ ነው እሚያረፍድ! እርስ በርስ እሚተራረድ!

ፉፉ : እኔ እገረ ሸረሪት አልቀር።

/ሦስቱም/ ኧረ ግናችንም አንቀር።
አሁን ይብቃን ይብቃን፣ ጠቅር ፈልጉ እንዳያጣን፣
ቀና ግም ነው፣ ግም ቀና ነው፣ ይጢስ ከርቤ ድኝና ዕጣን፣
ባየር በረን ከደፍ እደፍ፣ በጉም በረን ከደፍ እደፍ፣
አንጡዝንም ለግናደፍ.....
አንሰለችም ለግናደፍ.....
-/ዳንኪረዋች"መች ይሆን/ኧረ መች ይሆን/" በሚል የዛር ፈረስ ጭፈራ"አገውኛ" እየደነከሩ ይወጣሉ። ነጥብ መብራት ነጋ ላይ ሲበራ"የአግማን መቀነት" ሥነ-ግጥም ይዋነያል።/

ነጋ : የአግማ ኢትዮጵያ መቀነት፣ ቀስተደመናው አጠረ
የአንጀቷ ግሥሪያ ገመድ፣ እንደሸቦ አጥር ከረረ
መቆረረጥ አስመረራት፣ አስለቀሳት አስለቀሰኝ
ብረት መቀነት አንጀቷን፣ በጠሳትና በጠሰኝ
እቴ እመዮቴ አመመኝ
እንደ እሳት-አለንጋ አንጀቴን፣ እንደ ሲኦል አነደደኝ

ባክሽ ከመሄድሽ በፊት፣ አንድ ጊዜ ቁስሌን ዳሺኝ:.....
ያንቺን እኔ እንዳየሁልሽ፣ እይልኝ እንጂ አትይብኝ።

እሀቴ ቂም ብታገባ
ከአጥንቴ ወጣ ደም-እንባ
ሕዋሴ-ምፅዓት አነባ።

እንጂ እንርገም በአፈ-ቡካይ፣....
ለእናት ለአባት ለአድባር አዋይ
ሊሥርወ-ታሪክ አትበት፣ ይኸው ቃል ለምድር ለሰማይ
ለዘለዓለም ላንለያይ!

-/ቢ. አራጋው ድንገት ይገባል። ያንባርቃል።/-

ቢ. አራጋው መሸ! ነጋ፣ ጠባ፣ ዳግመኛም መሸ! ዳግመኛም ነጋ! ዳግመኛም ጠባ!....
አሁንም እዚሁ ነህ?!.....ለምን አትሄድም?

ነጋ : ያባቴ ቤት እኮ ነው። ያያቴ ቤት እኮ ነው።

ቢ. አራጋው ምን ማስረጃ አለህ?!

ነጋ : ደሜ። ተወላጅነት ደሜ። ደሜ ነው ማስረጃዬ።

ቢ. አራጋው ሰነድ እንጂ ደም አይቀርብም ለማስረጃ።

ነጋ : ደም እንጂ፣..... እንዲያውም ያንተ ሰነድ አይታመንም።

ቢ. አራጋው ያንተ?

ነጋ : ያንተ የቢ. አንጋጋው-አናጋው -አምታታው።

ቢ. አራጋው አምታታው ብትል በከንቱ ወሬ በቧልት፣ ያለተጨባጭ ሰነድ አምትረታኝ መስለህ?!...ኧረ
እንዲያውም አስቀድሞ ነገር አንተ ማነህ?!

ነጋ : ሕዝብ።

ቢ. አራጋው ሕዝብ?! አንተ ነህ ሕዝብ?!....ሕዝብ ማለት ምን ማለት ነው እንግዲያማ?!

ነጋ : ተንቀሳቃሽ ኃይል። እሳታዊ ፍቅር። ውቅያኖሳዊ ሰላም። ኃይል-ፍቅር-ሰላም።
የግንባሩን ላብ እንጠፍጥፎ የሚያድር። ተፈቃቅዶ፣ ተከባብሮ፣ ተግባብቶ፣ እርስ በርሱ
ተጠቃቅሞ፣ በእኩልነት አብሮ የመኖርን ጥበብ የተቀዳጀ። ሕዝብ ማለት ሰላም ነው።

ቢ. አራጋው ታድያን እንዴት አንተ አንድ ግለ-ሰብ ሕዝብ ነኝ ትለኛለህ?!

ነጋ : የሕዝቡን ሰቆቃ ስለምሰቀቅ። ደስታውን ስለምደሰት። ተስፋውን ስለምመኝ። ዓላማውን
ስለምከተል። ሕይወቱን ለመጠበቅ ሞቱን ቀድሜ እኔው ራሴ ስለምሞትለት። እኔ የሕዝቡ
አንድ ወጥ አከላቱ ነኝ። ሰውነቱ።....አንተስ ምንድነህ?

ቢ. አራጋው ቀድሞ ነገር እንዴት አንድ ግለሰብ እኔ ሕዝብ ነኝ ይላል?!

ነጋ : እንግዲህ ይብቃሃል። ዛሬ ጠያቂው እኔ፣ ተጠያቂው አንተ ነህ።....ባንተው ያራዳ
ፈሊጥ፣ ዘመንህ አክትሟል፣ አኪሩ ዞሯል፣ አደለም እሚባለው?

ቢ. አራጋው ነው። ብቻ አኪሩ፣ አሁንም እንደገና፣ ደሞ ይዞራል። አሁንም ገና ይሽከረከራል!

ነጋ : እስከዚያው ድረስ እኔ ጠያቂ፣ አንተ ተጠያቂ ነህ!....እና፣ ወንድሜ፣ አንተ፣ምንድነህ?

ቢ. አራጋው እኔግ እኔ ቢ. አራጋው አረጋጋው--

ነጋ : -- አንጋጋው! አናጋው!አምታታው!

ቢ. አራጋው አምታታው ብትል በከንቱ ወሬ በቧልት፣ ያለአንዳች ሰነድ እምትረታኝ መሰለህ?!

ነጋ : በደም!በውልደት! በቧልት ሳይሆን በደም ምስክርነት!

ቢ. አራጋው እሱንማ ሰምተናል!በእናትህ ግማሽ ትግራይ ግማሽ ወሎዉ ከሰሜን ወሎ ቦረን እስከ ደሴ ዙሪያ ኡርጌማ ክልል በግልጥ የታወቅክ! በወንድ አያትህ በአምሳ አለቃ ማሌ አያንሣ፣ ደቡብ ሲዳሞ ኦሮሞ ነገሌ ክልል በግልጥ የታወቅክ! በሴት አያትህ በገዛ እናቴ በጌጌ አምበርብር የሸዋ አማራ በሰላ ድንጋይ ክልል በግልጥ የታወቅክ! ምን አንተ ያልታወቅክበት የጉሣ ክልል አንድም አኮ የለ! እሱንማ ሰምተናል! ብቻ ከንቱ ወሬና የቧልት አሉታ ሕገ ዳኛ ፊት ፋይዳ አይፈይድም እንጂ!

ነጋ : ፋይዳ?!

ቢ. አራጋው አይፈይድም።

ነጋ : ደም ፋይዳ አይፈይድም?!

ቢ. አራጋው እሱም ቢሆን ገና ተመርምሮ ነው። የደምም ፋይዳነቱ በአዋቂ ሀኪም ገና በጥንቃቄ ተመርምሮ ነው። በቀጭን ረጅም ሲሪንጋ መርፌ ደምህ ተመጥጦ፣ሽቅብ ቁልቁል ተቀድቶ፣ ልዩ ላቦራቶር ምርመራ ገብቶ፣ የአማራ ደምህ ከትግራይ ድምህ፣ የኦሮሞ ደምህ ከአማራ ደምህ፣ ተፈልፍሎ ገና ተመርምሮ ነው።

ነጋ : -/ደረቱን ከፍቶ እጆቹን ዘርግቶ ራሱን እያቀረበለት/-እንካ እንግዲያማ ደሜን ቀድተህ ውሰደው! እንካ! እንካ ደሜን ከውስጤ አስመጥህ ከፋፍለው! ይቻለኛል ብለሀል ይቻልህ እንደሁ እንካ ውሰደው! ከፋፍለው!እንካ ወንድሜ!እንካ!!

-/ነጋ በከፍተኛ ንዴት ግሎ መሬቱን ይጐሽማል፣ ጠረጴዛውን ይረግጣል! እንደጋማ ኮርማ ይርበተበታል። አልጋና ምድጃውን የፈራርሳል። በዚሁ መሀል ዳንኪረኛ ቡድን ወላኢትኛ እየደነከረ ይገባል።/-

ወላኢትኛ ዜማ:-እንካ!!
ወንድምዬ!እንካ ድሜን!
ልቦናህን፣ ካፈረጠምክ
አድባር ከረገጥክ!
እንካ ሥጋዬን።
ወንድምዬ! እንካ ደሜን!
ልቦናህን ካፈረጠምክ
አድባር ከረገጥክ፣
እንካ!!

-/መብራት በቅፅበት እየጨለመ ዳንኪረኞች ይወጣሉ። ነጋ በነጥብ መብራት ተከቦ የአድባርን ጥሪ ሥነ-ግጥም ይዋነያል።/-

አድባር:-የኢትዮጵያን አድባር መርገጡ
ለፍካሬ ኢየሱስ ትንቢት፣ ለእልቂት ነው መቅበጥበጡ?
ዘለአለማዊን አድባር
ዘለዓለማዊን አውጋር
የኢትዮጵያን ሰፊ-ሕዝብ ውል
የአፍሪካን ታላቅ ቤት ባህል
እምቅድመ መሠረት ንግርት
ያባቶችን ጥብቅ ትእምርት
የሕዝባዊነትን ትንግርት
የሰውን ዘር መነሻ-ምርት
ጥንተ-ምሥጢር
ረቂቅ ቅምር
መርገጥ
ለመተላለቅ መቅበጥበጥ
የመጪረሻውን ምፅዓት
የፍካሬ ኢየሱስ አባት

ሲኦል ጥሪን ነው ግጋጋል
ግባባስ ነው ፍፃሜ ቃል!

-/ገደይ ትገባለች። ነጋ የሚፅፍበትን ደብተር ትነካለች። ትዳስሳለች። ትጠይቃለች።/

ገደይ : ፍፃሜ ቃል?

ነጋ : አዎን ፍፃሜ ቃል።-/ደብተሩን ይነጥቃታል። ትሰቀቃለች። ረዥም
ፀጥታ። መብራት ይፈካል። ገደይ እንደተሰቀቀች ኩርትም ብላ ትቀመጣለች። ረዥም
ፀጥታ። ነጋ ትዕይንት ተረት ይዋነያል።/-

ትዕይንት ሦስት

ተረት

ነጋ : አትሰቀቂ። -/ፋታ/- እኔም እንዳንቺ በሰቀቀን ነው ያደግኩት። ወሎ ቦረናን የቸነፈር ዶፍ፣ እንደጥብ እንሣ አሞራ መንጋ፣ ሺህ አእላፍ ጥፍሮች አግጠ፣ ዕልመት ምዕዐቱን ከሰማይ ቁልቁል ከመሬት ሽቅብ በቅዕበት ሲያሰፍንባት፣ አባቴ ሰሙ ንጉሥ ኩራዙን ይዞ፣ ወላጅ እናቴን እየጐተተ፣ ከአዘቦ ውቅሮ ራያ ቆቦ ዋልዲአ ላጉ፣ ከባቲ አውሣ ዋራኢማና ያልተንጠራወዘበት ያልተንከራተተበት፣ ሀሩር ያልለበለበው ችፍርግ ኩርንችት ምድር ተምች በዓይናቹ ያልተጀነጀነበት፣ አንድም ሰው አንድም ሥፍራ አልነበረም። -/ረዥም ፋታ/-

ያኔ፣ ዐደዬ እናቴ ደሞ፣ እንዲህ እንዳንቺ ወጣት እስክስተኛ ነበረች። ገና ያባቴ ተማሪ ሳለች፣ በልጅነቷ እንደወፍ አምትበር ተወርዋሪ ዳንኪረኛ ነበረች እናቴ እኮ፣ እቴ ገደይ። በራሪ ቆንጆ!...-/ትካዜ ትኩረት ልሣን/-....ቁም ሲኦል ግለት ምን እንድሆን ታውቂያለሽ? ቁም ሲኦል ግለት አየሽ፣ ፊደል ገበታ ልሣን በሣር ጠቁመሽ መግበሽ፣ በኩራዝ ጭምር በሌሊት ሀሁ አስቆጥረሽ፣ ጣር አሣር አይተሽ ያሳደግሻቸው እምቦቅቅሎች፣ እጆችሽ ላይ በድንገት፣ ኡኡ ራብን እያሉ ኡኡ ጠማን እያሉ እንደቅጠል ሲረግፉ ሲረፈረፉብሽ ነው፣ የስደተኛ መምህር ቁም ሲኦል ግለት!.....-/ፋታ-ሽኩሽኩታ ምሬት/.... ያባቴ ተማሪዎች፣ ወጣቶች ሕፃናቱ፣ እፊት ለፊቱ ዓይኖቹ እያዩ፣ በቸነፈር ተረፈረፉ። ምድር እንደቧጠጡ፣ አፈር እንደነከሱ፣ ዓይኖቹ ፊት ፈረሱ።....አባዬም ይሽን መዓት ያየበት ዓይኑን ጨፍኖ፣ ከርችሞ፣ ፊደሉን ደፍቶ ኩራዙን ጥሎ እርቃኑን ተሰደደ። -/ፋታ/- በረሀብ ሲኦል ምድሪቱ ስትጋይ፣ ወሎ ቦረና በእቶን አለንጋ ስትርገበገብ፣ አባቴ ሰሙ ንጉሥ ፊደሉን ደፍቶ ኩራዙን ጥሎ እርቃኑን ተሰደደ!!

.....-/እጅግ ረዥም ፋታ። ትካዜ ልሣን/-....

እኔ ያኔ ገና በእናቴ ማህፀን ነበርኩ። ሳልወለድ ነው አባቴ ሰሙ ንጉሥ፣ ከደሴ ዙሪያ ኡርጌሣ ከልል፣ ከሞት መንጋጋ አምልጠው ላያመልጡ በሞት ዳርቻ ያቃትቱ ለነበሩ የዕድሜ ትራፊ ተማሪዎቹ ቶሎ የዕርዳታ ስንዴ ልለምን ብሎ፣ ወደ አዲሳባ እዚችው ኣሁን እተቀመጥንባት ቄራ ከተማ፣ እዚችው አለንባት የእናቴ የእመት ጌኔና የአባቴ የአምላ አለቃ ጣሴ ቤት የተመለሰው። የዛሬ አሥራ ሰባት ዓመት ተመንፈቅ።

አባቴ በሌለበት እኔም ኡርጌሣ ላይ ተወለድኩ። ደሴ ገራአዶ ዙሪያ የዛሬ አሥራ ሰባት ዓመት ተመንፈቅ።

ከወተት ይልቅ በእስክስታ እሸሩሩ ወተቷ፣ ከአንቀልባ ይልቅ በእዝል ሙዚቃ እቅፍቿ አዝላ፣ በበራሪ ዳንኪራ ቆሌዋ አንከባክባ፣ ዓደዬ አሳደገችኝ። ዓደዬ እናቴ እንዲህ እንዳንቺ እስክስተኛ ነበረች እቴ ገደይ። -/ነጋ ከረን ከበሮ ጭፈራ ሲያጓጉ ገደይ ትጨፍራለች። ዳንኪራ ቡድን ያጅባታል። ነጋ ይፅፋል። ዳንኪራ ቡድን ይወጣል። ነጋ "ዐደዬን" ሥነ-ግጥም ይዋነያል።/-

ዐደዬ አየር ቀዛፊ
በወስፈንጥር ኮሪአግራፊ
ተንሳፈፊ፣
የእኩልነትን ብልጭታ
ለተራቡ ዐይኖች እይታ
በእጥፍ-ዘርጋሽ እንዳአለንጋ፣ተወርወሪ ሎሚ አፍታ፤
በቅዕበት ቅዕበት ብረሪ፣ ተስፈንጠሪ አፍታ ላፍታ

በዳንኪራ ተአምርሽ
በከበር መፈንጥቅሽ
ተደንቀሻል
ዓለምን አስተንግረሻል፤....
ይሁንና ተጠንቀቂ
በሰው ዓይን ፍንጣቂ
በቀሚስሽ ተደናቅፈሽ፣እርምጃሽን እንዳትለቂ፣
ተጠልፈሽ በራስ አድናቆት፣ ከመድረክ ጫፍ እንዳትወድቂ
ንቂ
ሽንጥሽን አታወፍሪ፣በጭብጨባ አትሠረቂ

የሙዚቃሽን ስልት ምት፣ እንደጀመርሽ ጠብቂ።
ዐዲ ዐደዬ አዲትግራኡት
የአክሱም ፀሐይ ርችት ብሥራት፣
ዐዲ ሥሪት
ዐዲ የወረብ ምት ሶፊት
በከበሮ ባህር ማዕበል፣ እንደመርከብ ተንሳፈፊ
በዳንኪራ መስፈንጥር ስልት፣ እንደተርብ አከናፍ ክነፊ
በፀናፅል አእዋፍ እዝል፣ አየር ላይ ነፍስ ቅዘፊ
በፒልካን ምት እስክስታ፣ ተወርወሪ ተወንጨፊ
.....ይሁንና ተጠንቀቂ።

- መብራት ይጨልማል። ይበራል። ቢ.አራአጋው በቅጣ ነጋ በቅዛዜ ስለዲሞክራሲ ይከራከራሉ።/-

ትዕይንት አራት

ዲሞክራሲ ጨቅላ

ቢ.አራጋው : ተበጥብጠህ ታውቃለህ? ብጥብጥ ብጥብጥ ብጥብጥብጥ ነው ያልኩት!

ነጋ እንኳን ደስ አለህ።

ቢ.አራጋው በገዛ አገርህ ሁለተኛ ዜጋ ሆነህ ታውቃለህ?

ነጋ እኔ ሆኛለሁ።

ቢ.አራጋው በገዛ ግዕድህ ቀለዋጭ ሆነህ ታውቃለህ?

ነጋ እኔ ሆኛለሁ።

ቢ.አራጋው ሞት አይሻልም?

ነጋ ለዚሁ ነው ታጋይ የሆንኩት።/ፋታ/-አንተስ?

ቢ.አራጋው ስለ ጦረኝነት ያለኝን አቋም ነግሬሃለሁ።

ነጋ ዲሞክራሲ ያለትግል፣ ከሰማይ እንደመና፣ ይወርዳል ያልከኝን ነው?

ቢ.አራጋው እንደ ግሀትግ ጋንዲ። የጠላትክን ደም ጠብታ ሳታደግ፣ የዲሞክራሲን ጅረት፣ በትእግሥት ኃይል ብቻ፣ በመስዋዕትነት ብቻ ማቋረጥ መቻል።

ነጋ እንኳን በትእግሥት በትግልም አላቋረጥን። በታሪካችን፣ የዲሞክራሲን ጅረት፣ ያቋረጥንበት ግዜ የለም።

ቢ.አራጋው የለም?!

ነጋ እንደነጋንዲ ትዕግሥታዊ ፀጥ-ለጥ መስዋዕተኝነትም ሳይሆን፣ ወይም እንደኛ ዛሬ የትግልና የደም ተጋድሎም ሳይሆን፣ የዲሞክራሲን ጅረት ያለማቋረጥ ችግር፣ ከመሠረ ባህላችን የወረስነው ነው። ደረስን ስንል ወደ ኋላ ይጐትተናል። እንድመቂናጥ። ማቋረጡን መጀመር፣ ሳይሻገሩ ከወንዝ መሀል ወደ ኋላ መመለስ፣ አንድ ትውልድ ሙሉ ፈጅቶ አስፈጅቶ ደሞ ሀ ብሎ እንደገና ለማቋረጥ መጀመር፣ ደሞ ሳያቋርጡ ጅረት መሀል መሰንከል፣ ወደ ኋላ መመለስ፤ የኢትዮጵያ ማሕፀን ጉደሎ በቀር ሙሉ ሰው መውለድ መቻል ስላቃተው ነው።

ቢ. አራጋው አንተ ጉደሎ ነህ? እኔ ጉደሎ ነኝ?!

ነጋ ክፉ ውርሳችን ነው ጉደሎ ያረገን። ወንድማችንን መንቀፍ ነው እንጂ መውደድ ችለንም አናውቅ

ቢ. አራጋው አንተ እኔን መውደድ አትችልም?! እኔ አንተን መውደድ አልችልም?-አለመቻሌን በምን ታውቃለህ? በምን ታውቃለህ?

ነጋ እናታችን ኢትዮጵያ ባህላዊ ሾተላይ ናት መሰለኝ። ዲሞክራሲን በስድሳ ሰድስት ወልዳ በላች። አስቀድሞም በእምሳ ሶስት አስጨንቃታል። ብትወልደውም ብትገላገለውም በዘለዓለም እያድግላትም። የማሕፀን መርገምት አለባት። በስድሳ ስድስትማ ወዲያውኑ ማግስቱን "አብዮት ልጆቿን ትበላለች" ብሎ ሊድከርላት የዲሞክራሲ ሾተላይ እናት፤ በላዔ-ሰውነኛ፣ መላው የዓለም ሕዝብ አስጠንቅሮ አወቀላት። -/ፋታ/

ቢ. አራጋው ዛሬስ? ዛሬስ?!

ነጋ ዛሬም አዲሱ ዲሞክራሲ ከተወለደ ገና ዘጠኝ ወሩ ነው። የሾተላይ ጥሪቷ ዳግመኛ እንዳያገኝ፣ በሕፃኑ ልደት ቀን፣ ቤተሰቦቿ ካሉበት ተሰባስበው፣ እንትፍትፍ አሰኝተው በመሀላ ቃል ገዝተዋል። የሕፃኑ እርግብግቢት ገና በአራሱ፣ በሾተላይ ዓይኖቿ ተወግቶ እንዳይፈርስ፣ ባህላዊ እብሪተኝነቷ መልሶ እንዳይነክስ፣ ቃለ ምህላዋ እንዳይረክስ፣ ወንድም ወንድም ላይ እንዳይነግሥ፣ ጨቅላ ዲሞክራሲያችን አራስ ብሌኑ እንዳይፈርስ፣ ቤተሰቦቿ

በተሰበሰቡበት ዕለት፣ በምህላ ቃል ገዝተዋታል።....እና እናታችን በግዝት ተይዛለች። እንደልማዱ ደሞ ውልፍጥ እንዳትል ብለው። በረሀ አቀፍ ልጆቿ፣ በረሀ የቀሩትን የታጋይ ሙታን ጓደኞቻቸውን ታሪክ ስምና ዓፅዕምት እያስታወሱ፣ ሚካ ለበስ ልጆቿች፣ አሸዋ አቀፍ ልጆቿ፣ስደተኞች ልጆቿ፣ በትግል የተሰየሙበትን የታጋይ ሙታን ጓደኞቻቸውን ስምና ዓፅዕምት በምኞት ረስተው የሥልጣን ሰይጣን እንደደርጉቹ በዛር ፈረሱ ሳይሠፍርባቸው፣ በሕሊናቸው የጋራ እናታችንን በትዝታ አቆራኝተው በግዝት ይዘዋታል። የአሥራ ሦስት ወሩን የዲሞክራሲ ጪቅላ፣ በሾተላይ ዓይኖቿ ወግታ ዓይኑን እንዳታሳውር።

ቢ.አራጋው — አይካካዱም ማለትህ ነዋ?

ነጋ — ልጆቿ?

ቢ. አራጋው — የተሰባሰቡት ቤተሰቦቿ?

ነጋ — ቃለ-ምህላ አፍርሰው?

ቢ.አራጋው — የሥልጣን ሰይጣን የዛር ፈረሱን አስፍሮባቸው?

ነጋ — እስካሁን ድረስ የልክፍት ምልክት ታየባቸው ትላለህ?

ቢ.አራጋው — ላንተ ባይታይልህ ይሆን?

ነጋ — ላንተ ታይቶሃል?

ቢ.አራጋው — ላንተስ፣ ጪልሞብሃል?

ነጋ — ሰው ሁሉ የሌላው ሰው ጉድፍ ነው ጉልቶ እሚታየው። የራሱ ጉድፍ አይታየውም። ለማሻሻል እንዲቻል ለዚህ ነው መጠየቄ።

ቢ.አራጋው — ጉድፍ የሌለበት ሰው የለም?

ነጋ — ሰው ሆኖ?!

ቢ.አራጋው — ሰው ሆኖ?!!

ነጋ — ያማ ሰው አይደለም ማለት ነው።

ቢ.አራጋው — እንግዲያስ፣ አንተ የራስክን ጉድፍ ከውስጥህ አውጥተህ ዘርግፈህ፣ እኔም የራሴን ጉድፍ ከውስጤ አውጥቼ ዘርግፌ፣ ፊት ለፊት እናስተያያቸው፣ እና ነፃዕራቸው ማለትህ ይሆናላ?

ነጋ — የራሳችንን ዕድፍ አውጥተን እርስ በርሳችን ሳናነፃዕር፣ እንደክፉ ባህላችን በሌላው ጭንቅላት ላይ የእራሳችንን ዕድፍ ለመታጠብ አንቸኩል ማለቴ ነው።

ቢ.አራጋው — እንደ ኤላጦስ እንደአጉታችን?

ነጋ — እንደ ኤላጦስ እንደአባታችን!

ቢ.አራጋው — አብርሃም ሊንኮልን ምን እንዳለ ታውቃለህ?

ሁለቱም — -/በአንድነት/-"እንዳንዱ ሕዝብ አንዳንድ ጊዜ ማጭበርበር ትችላለህ። አንዳንዱን ሕዝብ ደሞ ሁልጊዜ ማጭበርበር ትችላለህ። ሁሉንም ሕዝብ ግን ሁልጊዜ ማጭበርበር፣ ከቶም አትችልም። "-/ረሹም ፋታ/-

ቢ.አራጋው — አንተ እኔን ለምን አታምነኝም?

ነጋ — አንተ እኔን ስለማታምነኝ።

ቢ.አራጋው — .....እኔ ተጠራጣሪ ሰው ነኝ። ግንንም አላምን።

ነጋ — ራስክንስ ታምነዋለህ?

ቢ.አራጋው እንደሁናቴው። እንደ አመጣው። "አይተነው ዘንዳ የሆነ እንደሆን!"

ነጋ እምትቆምለት ዓላማ የለህማ?!

ቢ.አራጋው እምሞትለትም የለኝም።

ነጋ ታዲያን አንተ ራስክን ሳታምነው፣ እኔን እንዴት እመነኝ ትለኛለህ?

ቢ.አራጋው .....ተጠራጣሪው ሰው ነኝ አልኩህ። እንዲያውም ጥርጣሬ የሚሏት፣ ያለችኝ አቋም እሷ ብቻ ናት።.....እኔ እንዳንተ እንደአንተው እንደባለዒላማው፣ ግልጥልጥ ግልጥ ብሎ፣ እንደሰንደቅ ዓላማ ልቤ መሀል ተተክሎ፣ በይፋ አይውለበለብብኝም አቋሜ። ፍንትው ብሎ አይታየኝም። ሰንደቅ ዓላማ፣ አገርና ዒላማ ይድብለቀለቁበኛል። ዩሐንስም በመተማ፣ ኃይለሚካኤልም በማይጨው ተሸንፉ እንጂ፣ ለአንድ ሰንደቅ ዓላማ ቆመዋል። ለአንድ አገር ታግለዋል። ግለኛ ዓላማቸው ግን እየቅሉ ነበረ። ታድያን እኔን አንድ የአዲሱ ትውልድ ተጠራጣሪ የአራዳ ምስኪን፣ ሌሎች ለቆሙለት አንድ ሰንደቅ ዓላማና ለተለያዩበት ሁለት የተለያየ የትግል አቋም፣ እንዴት መትለት ትለኛለህ?

ነጋ ባጭሩ አቋመ-አልባ ነኝ፤ ለምንም ግብ አልዋጋም፤ እኔም እንደፈረንጆች የውጊያ ሁሉ ሕሊናዊ ተቃራኒ፣ ኮንሽኤንሽስ ኦብጀክተር ሆኛለሁ አትለኝም!?

ቢ.አራጋው አይነካካኝም። የጠረኝነት ሕሊናዊ ተቃርኖ የሚሉ ጣጣ፣ ባገሬ ባህል ትርጉም የሌለው ሀኬት፣ እኔ የለብኝም። አይነካካኝም። ይነካካኛል የሚል ሰው ካለ ደሞ፣ ባገሬ ባህል ኮንሽኤንሽስ ኦብጀክተር ፣ በአጭር ትርጉም ፈሪ፣ በረዥም ትርጉሙ ግን ያው ቦትቢቃ ነው።

ነጋ ይሽ ከሆነ እንግዲያማ፣ አንተ ምንድነህ?

ቢ.አራጋው ያቺን አሮጌ ጥያቄህን እንደገና ጠየቅካት።

ነጋ አንተም ባሮጌ ዘዴህ መልሷን ዘለልካት

ቢ.አራጋው አልዘላትም! አልዘላትም!

ነጋ ታድያን አውጣታ፣ ካልዘለልካት አውጣታ! ምንድናት ያንተሪ ዒላማ!

ቢ. አራጋው መኖር። መኖር ብቻ ነው የኔ ዒላማ። መሞት መሞቱን ላንተ ትጅልህለሁ።

ነጋ ተባይ። የሰው ተባይ!

ቢ.አራጋው -/በዛቻ/-አይ! አይ!!

-/ነጋ መሣሪያ ሲጨብጥበት ወደ ጓላ ያሸገሽጋል። ጉራንኛ ዳንኪራ እየገዘፈ የሚገባው ዳንኪራ ቡድን የሚቀጥሉትን መሥመሮች በመጠቀም ነው።/-

ጉራንኛ ገዘፋ:-አይ-አይ-አይ-አይ
ተባይ-ተባይ
አይ-አይ-አይ-አይ
ተባይ-ተባይ

-/መብራት ይጨልግል።/-

/ፋታ። መብራት ይበራል። ትዕይንት <u>ሳሎት አርም ቴራቲር</u> ይቀጥላል/

ትዕይንት አምስት

ሥስት እርም ቴራቲር

-/ነጋ እንደሰሙ ንጉሥ ተዋናይ ልብስ ለብሰል። ኩራዝ ይዟል/-

ነጋ ኧረ ምኑን ቴአትር ሠራነው?! እኛ ሁላችን በድፍን አጉል ቴራቲር ይሆነናል?! ዛሬ በኛው በቴራትረኞቹ ላይ ቴራትር እየተሠራብን ነን። በገዛ ሞያችን ተበለጠን ተበልተናል።

እኛ ተመልካች፣ ሕዝቡ ቴአትረኛ ሆነ። ፀጥተኛ ተመልካች። የሠራንበትን ያህል ሠራብን። ያውም ከኛ በባሰ የወቅት መክፈልት እንጀቱን ቋጥሮ እልቂቱን አልቆ፣ እንደኛ በጭራሬ እንደኛ በሽቀላ ሳይንገበገብ፣ በገዛ መድረካችን በነፃ ጥሪ መርገምቱን ተበቀለብን። አመቀብን። በዝምታው አላገጠብን። በገዛ ባህሉ እንደተጫወትንበት እሱም መልሶ ተጫወተብን። እንዲ ተመልካች፣ እንዲ ተደራሲ ህዝብ እንለዋለን ደሞ ይኸን ፈታኝ ታዛቢ በዝምታው ኮናኝ ሕዝብ! ነጋ ጠባ እንካ ጦርነት ብላ ጮማ ጮማውን ለኛ እንለዋለን!...ይሁንና ነቃብን። እሱ ቴራትረኛ ሆኖ እኛን አጨብጫቢ አደረገን። በገዛ መድረካችን በሞያችንበለጠን። እኛ ተጉታች ሬሞርከሮ ሆነን እሱ ቀደመን።

ዛሬ ከሕዝቡ የበለጠ ግንም ረቂት ቴራቲረኛ የለ። በቀል ነው። ግዘናጊያ እንጂ ሐቅ አንዋነይልህም አልነው። ሞያችን አዋረድንና ሞያችን አዋረደን። መድረክ መቅደሳችንን አረከሰነውና አረከሰን። ረገምነውና ረገመን። ለካስ ከሰው እርግማን የሞያ እርግማና አጥንት ይሰብራል። ያልከሰከሳል። -/ፋታ/- ቀድሞ ቤተ ክህነትን በዕፀ-ፋርስና በአብሽ ትፋት ያልኮሰኮሱ የደባትር አጣቢዎች፣ ዛሬ በጫት ዶክሲ ትፋት የመድረክ አልኮሰኳሾች ተተክተዋል። ከአባት ወደ ልጅ። ትፋት።

ክርስቶስ ሽቃዮችን በጅራፍ ገርፎ ካባቱ መቅደስ እንዳባረረ እኛም መርሮናልና ከሕዝባዊ ደጃችን ከመድረክ መቅደሳችን የጫትና ዘመናይ የሀሺሽ ሽቃዮችን በጅራፍ ገርፈን እናስወጣለን ብለን፣ የቁጣ እጆቻችንን ቃጥተንባቸው ነበር።.....

እጆቻችንን እርስ በርሳችን አቆላልፈው፣ ባለፈው ዘመን የሥነ-ጥበብ ሰውነታችንን አራቁተው፣ ክንዶቻችንን አነካክተው፣ ዛሬም እጀ-ለሆሳስ ልበ-ቀር አፈ-ቱልቱላ የቧልት-ቋት፣ እዚያው መለሰው አዝግሬ አድርገው፣ እንዳልሆነ አደረጉን።

እኔ ጅሉማ፣ አንድ ቀን እንደአባቴ፣ በልጅነቴ የተጠናወተኝን ስለ ተዋናዩ ሰው የዕድሜ ዕጣ ክፍል፣ በሥነ ጥበብ ሰውነት በሞያው ክብርና ደንብ፣ ለሕዝብ ሰላም ይዤ ጤና አዳም፣ በጥንቃቄ ለመወጣት አደገድጌ ታጥቄ ቆሜ ተለማምጀም ነበር። ስለተዋናዩ ሰው የዕድሜ ዕጣ ክፍል ታሪክ።...አልሆነልኝም።

የአባቴን የተዋናዩን የመምህሩን፣ የሩቅ ተጓዡን፣ ሰላም ጥሪ ፈጻሹን አንግቤ፣ ኩራዙን ይዤ፣ የአባቴን የሰሙ ንጉሥ ጣሌን የመድረክ ንጉሥ ሱሪ፣ እንደወንዶቹ አጥልቄ ነበር።

አልሆነልኝም።

ግን፣ እርም። ቃል ለምድር ለሰማይ! ከእንግዲህ እንደአባቴ ተዋናይ ነኝ ተብዬ መንፈሰ አርቃኔን ሕዝብ ፊት ቆሜ ያባቴን ሞያ አላሰድብም! መድረክ መቅደሴን አላዋርድም! አላስረክሰም! አልዋነይም! እርም!

ግን I ሕይወቴ እየለ ከእንግዲህ ወዲያ ደሞ፣ በጥበብ ሽፋን የጠይብ ተግባር፣ ያባቴን መድረክ በጫት ትፋተኞች አፍ ሰላም ፈላጊ ተመልካቹ ሕዝብ ላይ እርኩስት አላስተፋም!እርም! ! ቃል ለምድር ለሰማይ!

-/ኩራዙን ሊያጠፉ ይቃጣና ይተወዋል።/-

ግን፣-ሕይወቴ እያለ ከእንግዲህ ውዲ ደሞ፣ የሰፊውን ሕዝብ ዲሞክራሲና የሰላም ጭላንጭሉን፣ አላስነጥቅም! ሕይወቴ እያለ ያንን ይፅልመት ዓለም ዳግመኛ አላስደግምም!! እርም!! ቃል ለምድር ለሰማይ!

-/ኩራዙን ያጠፋዋል/- -/ትእይንተ ኤጭ ይቀጥላል።/-

ትእይንተ ኤጭ ይቀጥላል

ትዕይንት ስድስት

ኤጭ

ቢ.አራጋው — -/የእጅ ሬዲዮ ጆሮው ላይ ሎግሞ ተንደርድሮ ይገባል። የበሳጫል/- ኤጭ! -/ሬዲዮውን/-ምን ይቀባጥራል?! -/በብስጭት ይዘጋዋል።/- የዛሬውስ ዓለም አበዛው!....ዓለም እኮ የኛ ዕዳ አለበት።

ነጋ — ይልቅስ እኛ የዓለም ዕዳ ነን።

ቢ.አራጋው — የዓለም ታላቅ ከተሞች፣ ሎንዶን ኒውዮርክ ወይንም ፓሪስ የተገነቡት፣ በኛ በአፍሪካውያን ላቦት ደምና አጥንት ነው።

ነጋ — ላቦታችን ደማችን አጥንትና ሥጋችን የኛን ከተሞች እንዲገነቡ፣ ደግሞ መታገል ያለብን እኛው እራሳችን ነን። ሌላ ማንም አይታገልልንም። ሌላ ማንም አይገነባልንም።

ቢ.አራጋው — የፈረንጅ ዓለም እኮ ብዙ ግፍ ውሎብናል። አለበት ዕዳ!

ነጋ — እኛ በኛ ላይ የባሰ ግፍ ውለናል። እርስ በርሳችን አለብን የባሰ ዕዳ!

ቢ.አራጋው — አስቀድሞ እኮ ሥልጣኔ ለግሠነዋል ለዓለም።

ነጋ — ዓለም ደሞ በተራው ለኛ ሥልጣኔ ለግሦናል።

ቢ.አራጋው — ለችግራችን ባስቸኳይ መድረስ እኮ ይጠበቅበታል።

ነጋ — ዘለዓለም ከችግር እማንወጣ የምናሰለች ተመፅዋቾች እኮ ሆነናል።

ቢ.አራጋው — ታድያን በረሀብ ጭጭ ብለን እንለቅ?!

ነጋ — ለምኖ ብቻ መብላት ሣንሰራ ብቻ መብላት አላሣፍረን አለ! ይሉኝታ አጣን። የዓለምን ዓይን አወጣን።

ቢ.አራጋው — ኤጭ!

ነጋ — ኤጭ!ጠባብ!

ቢ.አራጋው — እባብ!-/ፋታ/- ከፉ የፈረንጅ ተሟጋች ወጣህ።

ነጋ — ከፉ ያበሻ የስንፍና ዛር ከነፈረሱ ተሣፍሮብሀል።

ቢ.አራጋው — እኛ እኮ የዓለም ሥልጣኔ መሠረተ-አባት ነን!

ነጋ — ሠለጠን ስንል ሠየጠን እንጂ! ሰምንት ሺ ዓመት ሠለጠን ካልን፣ ከዩጉዝላቪያም፣ ከአርሜንያም፣ ከሶማልያም፣ ይኸው የሥልጣኔ ከባድ ጥያቄ ተደቅኗል ፊታችን። ትልቁ ጉዳይ መለፍለፍ ሳይሆን ማለፍ መቻል ነው ፈተናችንን። ሠልጥነን፣ ተቻችለን በሰላም እናልፋለን ወይስ ሰይጥነን እርስ በርሳችን እንተላለቃለን?

ቢ.አራጋው — ጥያቄ እንደሆነ የጠየቅከኝ፣ እንኳን ያባቶቻችን ሥልጣን፣እኔ የኔም ድንቁርና አይገባኝም።

ነጋ — ዓለምን ያስደነቀ ያባቶቻችን ምጡቅ ሥልጣኔ፣ አይከሰስም፣ በኛ በጭንጋፍ ልጆቻቸው ብያኔ!

ቢ.አራጋው — ኤጭ!

ነጋ — ኤጭ!

ቢ.አራጋው — አስተሳሰብህ እንደፈረንጅ ሽሪንክ፣ አንጐሉን ተሸምቅቆ አንጐል እሚሸመቅቅ ሸማቂ ሳይካት ሪስት ዓይነት ሆነህል።

ነጋ — አንተ አንጉል ለሆሳስ፣ እንደጣልያኑ አባ ግስያስ፣ከሽሪንካ የባስክ፣ የምኒልክን መንግሥት ዓይን እንዳጠፋው፣ እውር ፈረንጅ ቄስ ነህ። ያበሻ አንጉል አናዛዥ። የአእምሮው ገናዥ። የአፍሪካ መሪዎችን ህልምና ሀሊና በዝባዥ። ለቴዎድሮስም ሊቀመኳስ ጆን ቤል፣ ለዮሐንስም ራሳም፣ ለተፈሪም ግስተር ዲስፔንሰር ነው፣ ለመንግሥቱም አነኢኛን ቭላዲሚር።

ቢ. አራጋው — እኮ እንደነፓል ሄንዚ?!ዘመናዊው የኢትዮጵያ ሽሪንክ? ኮንግሬስ ግንባር ቆሞ፣ "ኢትዮጲያን ግሯት! የለም አትግሯት! ኢትዮጵያን እርዱት! የለም አትርዱት! ግሯት! አትግሯት!" ሲል እንደሚወተውተው ቴክኖክራት ጠንቋይ ጨሌ ጣይ?!...እሱ ያንተ ሽሪንክ እንጂ የኔ ሽሪንክ አይደለም።

ነጋ — አታውቅም እንጂ አንተ ከሱ ሦሥት እጥፍ እምትብስ ነህ ወንድም።

ቢ.አራጋው — ብትወድም ባትወድም ፈረንጅ ሽሪንክ ዘለዓለም ዓለሙን ከአፍሪካችን አንጉል ላይ ፈጽሞ አይወርድም። የሀያ አንደኛው ከፍለ ዘመን ቴክኖክራሲ መዥገር ነው። የአእምሮ ላይ ጣበቆት።

ነጋ — ያንተ ብጤ ዴማጉግ ደሞ የሕዝብ ላይ ጥንብ አንሣ አሞራ፣ እኔ አውቅልህሀለሁ ባይ፣ የጉንዳን አውራ፣ ከሰውነትህ ሁሉ ጭንቅላትህ ያበጠ፣ ልክ እንደጉንዳን መሪ የራስክን የአንጉል ጭነት መሸክም እግትችል፣ መላወስ ተቸግረህ ሀፍረት ዳሌህን ወደ ሰማይ አቁመህ ባፍጢምህ ተፈግመህ አፈር ላፈር እምትድህ-

ቢ.አራጋው — ዝም በል ባክህ! በጉንዳን ጭንቅላቴ በድህ፣ ባሞራ ጥፍሬ ብጭር፣ ለዚች ላለቺኝ አንዲት ሆድ የእለት እንጀራ ልቃርም እንጂ፣ እኔ እንደዓለም ኃያላን ተደናቂ ጌቶችህ እንደቡሽ እንደጉርባቶቭ የዓለምን አቀግመጥ ልገለባብጥ እኮ አይደለም።

ነጋ — የዓለምን አቀግመጥ መገለባበጥ?!

ቢ.አራጋው — ፈላሾች ወገኖቼን ትላንት በቀውጢ ሰዓት፣ ከኢትዮጵያ አከላት እንደትርፍ አንጀት ባሰሉት ሜራ በጭቀው ቆርጠው፣ በክርስቶስ እንደለመዱት በሠላሳ አምስት ሚሊዩን ዶላር መላውን ጉሣ ሸጠው አስሸጠው፣ በረሀቡ ተጠቅመው ባዕድ አርቲፊሴል አካል ላይ ወሰደው በዘፈቀደ ተቀጥላ ቀጥለው፣ አንድ ነን ብለው እኩል ነን ብለው የእሥራኤል ቡርጂ አሽከርና ገረዶች አደረጓ ቸው።

ነጋ — ይኸን ግሰብ የነበረብህ ያኔ ቀደም ብለህ ካድሬ ተብለህ፣ ዩኒፎርም በሚባል ሰማያዊ የክር መወጠሪያ ካኪ ውስጥ ተሰፍትህ፣ ተወጥርህ፣ ተቀርቅበህ፣ በጭቁን ስም ሰላምን ግፍፈህ፣ ባናጠርክበት ወቅት ነበር! ቀድሞ። ዛሬ አይደለም። ...ዛሬ ላንቃህን ብታናፍረው ትርፉ የጉሮሮ ሮሮ ነው።

ቢ.አራጋው — ዛሬ? እውነትህን ነው፣-ዛሬ። -/ፋታ/- ዛሬ የሕዝባችን አፈ-ቀላጤ ምሁር መርሲነሪዎች የስነ-ልቦና ጦር ረቂቅ ቅጥረኞች፣ አፈ-ቱልቱላ የባንዲራ ደላላ፣ ቃለ-ዘበናይ እንደበቱ ብልጣ ብልጥ፣የሀብታም ፈረንጅ አሮጊት ቅምጥ፣ የሕይወት ዋስትናውን በሕዝብ ደም ሊሸቅጥ፣ አንድ እግሩን አማሪካ ሌላው አዲስ አበባ የሂልተን እልፍኝ ግልፍጥ፣ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ባቋራጭ ሥልጣን ሊያጥጥ፣ በቃሉ አይረጋ ልሣነ ግልብጥ፣ በቴሌቪዥን አጀብ ፈርጣም ጣቶቹን አቁለጭልጮ እሚያሸቃብጥ፣ አካለ ሙክት ትንፋሽ ኮኛክ ብስኩት፣ ኢንተሌክቿል እሚሉ ጄት በራሪ ጉጉት፣ ኮራፕሽኒስት ብቻ ያንተ ብጤዎች እንደተስቦ ያመጣችሁት፣ ባፉና በእግሩ ጭምር እንደዝንጀሮ ያስጨበጨባችሁት፤.-አዎን እሱ ብቻ ነው ዛሬ፣ ሕዝብ መካከል ኖሮ ችግሩን ያልተግረ፣ ድሮ ለረሳው ወገን፤ እሱ ብቻ ነው ዛሬ፤- አዛኝ ቅቤ አንጓች አፈ-ጡሩም ብቸኛ አፈ-ቀላጤ።

ነጋ — ሙጤ የመንደር አፈሙጤ። አንተ አትብስም አሁን በእግዚአብሔር፣ ሕዝብ መካከል ተወልደህ አድገህ፣ ደሀውን ረስተህ፣ ደካግ ጉኑን ተንትነህ አውቀህ፣ ለራስህ ጥቅም ብቻ ሕዝቡን ዘለዓለም የምትጋልብ፣ አንተ አትብስም የጭቁኑ ሕዝብ ጅብ? አንተ አትብስም?

ቢ.አራጋው — እንግዲያማ እስቲ በግልጥ እንደራደር። እኔ ነኝ አንተ ሕዝብ ሕዝብ እያልን ዛሬ፣ በጭቁኑ ሕዘብ ስም ራሳችንን·እምናድልብ?

ነጋ ዲሞክራ — -/አጭር ፋታ። ቁጣ ልሣን/-ታሪክ ይመስክር። ሕዝብ ይመስክር። ሰላም ነፃነትና ሲ ይመስክር።

ቢ. አራጋው — -/በተመጣጣኝ ቁጣ ልሣን።/ የአንድ ግለሰብ መብት በማንም ቡድን መብት አይረገጥም።

በኔም ታሪክ ይመሰክር። ሕዝብ ይመሰክር።....ለሕዝቡማ ስለምትቆጭ አደል፣ ዓለም ባለቸ ኳይ እርዳታ ይላክ ስልህ እኛ የዓለም ዕዳ ነን ብለህ ማለትህ!?

ነጋ ዕድሜ ላንተ ብጤ ሥራ-ጠል ስንብንብ ሣይሠራ ለሚበላ፣ ዛሬ ያገራችን ስም ኢትዮጵያ መባል ቀርቶ ለማኝ ተብሏል። በአዲሱ መዝገበ ቃል ተመፅዋች ተሰኝታል። ያለባህላችን። ያለስ ማችን። ያለአባታችን። -/ፋታ/-አባቶቻችንማ በረኃም ዘመናቸው አገራችንን የአፍሪካ ዳቦ ቅርጫት አስደርገዋት ነበር። አልፎ አልፎ ቢቸገሩም አባቶቻችን የውለታ ወሮታ ከፋይ ነበሩ። በችግራቸው ሲደርሱላቸው እግዚአብሔር ይስጥልኝን ያውቃሉ። እንዲያው ውጤ ቋልጭ አይሉም። ብድርም ይከፍላሉ። ያመሰግናሉ። ያንተ ብጤ ግን ከተም መስንብንብ በቀር ምሥጋና አይሰጥም።

ቢ.አራጋው ምሥጋና?!

ነጋ አዎን ምሥጋና!!-/ፋታ/- የዛሬውማ ሁሉም ካንተ ብጤ ተምሮ፣ የኔ ብጤውም ጭምር፣ በድ ምር ሁላችንም፣ ከዓመት ዓመት እጃችንን ዘርግተን ዕርዳታ አምጡ ከማለት በቀር፣ እንኳን ስ የረዳንን የተሰዋልንንም አናመሰግንም። እናስታውስም። ከአባቶቻችን ትህትና ቁም ነገር አልተማርንም። እኛ ገለታ ቢስ ነን። እንኳንስ የረዳንን የሞተልንን አናስታውስም።
-/ረዥው ፋታ። ጥሞና ልሣን/- ሚኪ ሌላንድን ታውቀዋለህ?

ቢ. አራጋው ኤጭ!

ነጋ "ኤጭ " ምንድነው?!

ቢ.አራጋው እኔ ሚኪ ሌላንድን አላውቀውም ማለት ነው!

ነጋ -/ፀጥታ። ትካዜ ልሣን/- እኔ ላንዲት ቅጽበት ደቂቃ ተዋውቄው ነበረ። -/ፋታ/- ታሪ ኩንላ አታስታውሰውም?

ቢ.አረጋው እኔ አላስታውሰውም!

ነጋ -/ረዥም ፋታ፣ ጥሞና ልሣን/- ገለታ ቢስ ነህ። እኛ አዲስ ትውልድ፣ ዓይናችንን ከርች መን መስንብንብ በቀር፣ የሞተልንን ማስታወስ አንፈልግም።

ቢ.አረጋው ኤጭ!-/ተፈናጥሮ ይወጣል።/-

-/ፋታ። ትካዜ ልሣን/- እየተሰነጠርን ኤጭ ማለት በስተቀር፣ እንደ አበቶቻችን እናመሰ ግንም።

-/ዳንኪረኞች በቢ. አራጋው መሪነት የአራዳ ብረክ ዳንስ እየደነከሩና የሚከተሉትን መሥመ ሮች እየዘፈኑ ይገባሉ/-

ኤጭ/:- ኤጭ!ኤጭ!ኤጭ!ኤጭ!
አየሩ ቀጭ!
ምድሩ መረጭ!
ትንሽ ሲመች፣ ሆ መፈንጪት!
ቅር ያለ እንደሁ፣ ሆ ራስ መንጪት!
አጉል ባህል፣ መወራጪት!
ኤጭ!ኤጭ!ኤጭ!ኤጭ!
አየሩ ቀጭ!
ምድሩ መረጭ?!

-/መብራት ይጨልግል። ፋታ መብራት ይበራል። ትዕይንት ፉኛዶ አምልክ ይቀጥላል።/-

ትዕይንት ሰባት

ፉኟዶ አምልኮ

-/በንጥብ መብራት ተከቦ፣ አስክሬን ሣጥን ፈት ለፈች ቆሞ፣ ሣጥኑ ቀኝ ጫፍ ላይ ቁጢጥ ብላ ለምታዳምጠው ለዳንኪረኛ ፉቶ የፉኟዶን ቀን ይተርካል። ቡና ያፈላሉ። ቆሎ ይቆላሉ። ቁጢጭ ያንጥፋሉ-/-

ለምን እኮ ነው ታዲያ፣ ከዓመት ዓመት ዘለዓለም ዓለም፣ በአንከር፣ በምሥጋና፣ ቦኟቾች ጀግኖቻችን ትዝታ ፈለግ በሀሳባችን ስንመላለስ የምንኖረው?

ሊጋንዲ ዕለተ ሞት፣ ለክርስቶስ ትንሣኤ፣ ለፑሽኪን ልደት፣ ለማርቲን ሉተር መታሰቢያ ቀን ወዘተረፈ-ዓይነቱን ግለትሽ ነው።

ዓይነቱን ግለቴ ነው።

ሰው ይሞትና፣ ወትትም ያልፍና፣ ትዝታው ብቻ እኮ ነው ሀሳብ ላይ እንደቅርፅ ትክን እያ ለ ሁሌም ለቋሚ እሚተርፈው ትርፍ።....መናኛ ሰው ትዝታ-አልባ ነው።....ተራራ የሚ ያክል ሰው ትዝ ሲልሽ ግን፣ ትዝታው ራሱ ያው ግዙፍ ተራራ ነው። እንደኦሚኪ ሮላንድ።

ፉኟዶ ኮረብታ ላይ፣ በፍንዳታው ቀን አጥንትና አከላቱ እንደፅልመት ደመና ሽቅብ ነዶ ተነነ። ያ ተራራ ሰው ዐመዳይ ሆነ።..... ከቃጠሎው መልስ ግን ጉዞ ፍታት ተፈታ። አውራ ጣት እግታክል ከሰል አከላት ብቻ ነበረች ለቀብር የተረፈች።....የቀረው ግ አከላት አፈር ድቤ ዓመድ የሎጥ ሚስት ጨው ትብያ ሆኖ ተነነ። ደቡብ ኢትዮጵያ ፉኟዶ ኮረብታ ላይ በነነ።.... ያቺን አውራ ጣት የግታክል ከሰል ነው፣ የሚኪ ሌላንድ አከላት ብሎ፣ ጀት አውሮፕላን በትልቅ እጀብ አሜሪካ ያገባው። ከዚያ ከተራራው ሰው አካል፣ አው ራ ጣት እግታክል ከሰል ናት የቀረችው።

"አንድ ሕይወት እኮ ግዳን፣ ዓለምን ሁሉ ግዳን ነው፣"ብሎ፣ ከሞት አፋፍ ላይ የነጠቃትን ሕፃን ልጅ በክንዱ አቅፎ፣ እንዲህ እንደኔ በወንድ ድኩም መዳፍ ጨቅላዋን አዝሎ፣ እጅግ ከባድ ብቸኛ ሸክም ልጁን በጥርሷ ይዛ ቀየዋ ተቃጥሎባት መድረሻ እንደጠፋ ባት ጡቶጅ እንደደረቁ ከርታታ ወላድ ድመት፣ ያቺ አንድ ሕፃን ሕይወት ሚኪ ሌላንድ እቅፍ ውስጥ በቅጽበት ሞተችበት።.....እንዲህም አርጉ ምፅት ፍልብፍና የለ አቦ፣"አንድ ሕይ ወት ግዳን ዓለምን ሁሉ ግዳን ነው"ብሎ"!....ዋ! እንኳን ዓለምን ሁሉ ሊያድን የአንዱ ንም ሕፃን ሕይወት አጣት!

ያም ይሁን እንጂ ሁለት እጆቹን ዘርግቶ፣ አሜሪካ ኮንግሬስ መካከል ገብቶ እንደ ክርስቶስ በቃሉ-ኃይሉ የውበት ልዣን ብቻ ከዐለት ልቦና ቅቤ እያወጣ፣ ሚኪ ሚካኤል የዓለ ምን ሁሉ ለማኝ ዘር ሕፃን ዳቦ መገበ። የራሱን ሕይወት ጥምር በፉኟዶ ኮረብታ መስዋዕት ዳቦ ሰጠ። "የራሱን ሕይወት ለሌሎች አሳልፎ ከመስጠት የበለጠ ፍቅር የለም ፣እውነትም። እኔም ከዚያች ዕለለ ቀን ወዲህ ነው እንደዚህ እንዳሁኑ የሙት ዓመቱን በአባቶች ሥርዓት ፍትሀት ላስፈታ ስሙን ላስጠራ ለሀሊናዬ መሃላ የገባሁት።

ከሰው ዘር አንዳንድ ሰው ለአንዲት ቅጽበት አይተሽው ገፅታው ሕሊናሽ ላይ ዕድሜ ልክ ይታተማል።

ሚኪ ሌላንድን በቀውጢ ዘመን ትግራይ ረሀብተኞች ካምፕ፣ አግኝቼ ተዋወቅኩት። ለአንዲት የደቂቃ ዕድሜ። ገፁ ለዘብታ ለበስ ንቁ፣ መንፈስ-ይፋ ፈጥኖ ተቀራራቢ፣ የዐይኑ ስለት ግን አንጣጥሮ ልቦና ይወጋል። ይጠይቃል። ይፈትናል።.... በዚያች በአንዲት የደቂቃ ዕድሜ፣-ዛሬ ትዝታው መላልሶ ትዝ ሲለኝ፣-አንዴት እንደሆነ በግልጥ ባላውቀውም፣ ዕድሜውን ሙሉ የሰዎች ከሀደት የታከተው ነበረ ሚኪ ገፅታው። አንቲም ሰው ተመስለህ ነገ ሕዝብህን ትክደው ይሆን፣ የሚል ጠያቂ ነበር ሚኪ ገፅታው። ይህንን ነበር ሳያናግረኝ በገፁ የጠየቀኝ። የሰዎች ከሀደት በታከታቸው፣ በአንጣጥሮ ልቦና ወጊ ዓይኖቹ።..ለዚህ ሳይሆን አይቀርም፣ በኔና በቢጤዎቹ፣ የፉኟዶ ኮረብታ መታሰቢያነት፣ ትዝታችን ላይ እንደሀውልት የሚጉላው። ይሽ ትዝታ በሰው ልጅ አመጣጥ ታሪክ አዲስ ቅሪትም አደል። ጥንትም አባቶቻችን ለእግዚአብሔር መታሰቢያ ኮረብታ ያመልካሉ። ለተራራ ያርዳሉ።.....የእሥራኤል አባት አብርሃም አርጉታል፣ ከጥንት አፍሪካውያን አባቶች ላይ ተምሮ። ለተራራ አርዷል። ሚኪ ለኔ ተራራዬ ነው።

ታዲያን ከፉኟዶ ታጠሎ መልስ ኋላ፣ እዚያው አሜሪካ መንደር ላይ የራሱ ቀየ ልጆች

በተሰበሰበበት፣ በአፍሪካውያን አሜሪካኖች የቀብር ውርስ ሥርዓት፣ በሙሾ ዋይታ በጥንት አባቶቻችን የጉዞ ፍትሀት፣ ያቺ እንዲት አውራ ጣት የግታክል አካላት፣ መቃብሩ ላይ እንደ ክርስቶስ ሥጋ-ወደሙ ዳቦ በመቁረስ ፍትሀት ተፈታች።

ለዚሁ ነው ዘለዓለም ዓለም፣ ቦኟቾች ጀግኖቻችን ትዝታ ፈለግ፣ በሀሳባችን ስንመላ ለስ የምንኖረው።

-/ነጋ በመቃብር ሣጥን ላይ ያለውን ዳቦ ይቆርሣል። ቡራኬ ለሕዝብ ያቀርባል። ዳንኪረ ኞች ልብሰ ተክህኖ ለብሰው፣ ፅናፅልና ፅና እያንቃጨሉ፣ ጉዞ ፍታት ዳንኪራ ይመርባሉ። የመቃብሩን ሣጥን የዩናይትድ እስቴትስ ሰንደቅ ዓላማ ያለብሳሉ። ፍትሐተ ፀሎት እያዜሙ ይወጣሉ።

-/መብራት ይጠፋል። መብራት ይበራል። "ትእይንት ባፍንጫዬ ይውጣ" ይቀጥላል።/-



ታጋይ ነጋ በሕዝብ መሀል ሩጫ ልምምድ

ትዕይንት ሰምንት

ባፍንጫዬ ይውጣ

ቢ.አራጋው –/ስልክ ይዘል። ጉርድ በርናስ ለብሏል።/– ባፍንጫዬ ይውጣ! ያንተ ምርጫ ባፍንጫዬ ይውጣ! ገንዘቤን ብቻ ! ገንዘቤን ቶሎ! ደሞ አስመርጥህለሁ ብለህ ገንዘቤን በልተህ ልት ተር! ያንተ ምርጫ ባፍንጫዬ ይውጣ! ያንተ ሲሞክራሲ፣ ያንተ ቻርተር፣ ያንተ ጭቁን ሕዝብ ያንተ ምንትስ፣ ባፍንጫዬ ይውጣ! ገንዘቤን ብቻ !አንጡራ ሳቤን!ገንዘቤን ቶሎ!..ሀ ሎ!ማነው?! እኔን ነው ማነው የሚለው?!ሀ ሁን አልቀጥርክም ወይ በለው!? ጋዜጠኛው ቢ.አራጋው! የጥሱ ናያው ግርፍ ነው በለው!ንገረው! የትላንቱን አስተውሰው!..... ሀሎ!...እኔ አልበላም ባክህ የሚበላ ይበላ በለው የኔ ብጤዎች የሽግግር አጋሠኞች ነን። ጀርባችን ሁሉን መሸከም ለምዷል። ከዘመን ወደ ዘመን! በሸክም ተለምጧል። ደርግም አሠልጥኖናል–አሠልጥኖናል። ዕድሜ ለቢርከራሲ ጡጦ ጠብተን ተለስቀን፣ መለስን ተመስለናል። ንገረው!አብሮ መዝለቁን ጉዑ ጠብቶ ግጥግቱን እንደ ጡት ልጆች ባህል ዛሬም አውቀንበታል። ያባታችን ነው። ተክነንዋል። ራሱ ይፈነቃቀል እንጂ እዚያ እርስ በርሱ እኛን ግንም አያፈናቅለን። ሠርፀንበታል። ትንታግ ታውቅ የለ! አይፈነቀል ትንታግ! ሀሎ!...ይልቅ የኛን ዘበናዊ ደበሎ፣ ዘበናዊ አጉዛ ኢንተርናሽናል ነፃ የበርናስ ግስታውቂያ ድርጅት፣ ስሙን እንዴት እንበለው?! በርናስ እስታይል?በርናስ ፋሽን? ወይስ በርናስ ሞድ?...ባክህ ዛሬ እግይሽጥ የለም፣ ይኸ ያዲሱ ዘመን ኢንተርናሽናል ግብስብስ ትውልድ ግገበስበስ እንጂ የመልበስ ጣዕም፣ የት ያውቅበታል፣ የት ይፈልጋል፣ የት ይገባዋል?! ይሸጣል ባክህ፣ ዛሬ እግይሽጥ የለም! አንተም ፐርሰንቴጅህን፣ቁጭ ብለህ ከኔ እኩል ታንክታለህ።.....ብቻ ያበሻ ገበያ ያው እንደመኪና አነዳዱ ነው። ለመንዳት ሳይሆን የሌላውን መንገድ ለመዝጋት። ለመነገድ ሳይሆን በሌላው በገበያ ላይ ለመገድገድ።...ሀሎ!...ባፍንጫዬ ይውጣ! ያንተ ምርጫ በፍንጫዬ ይውጣ! ገንዘቤን ብቻ!አንጡራ ሳቤን ሀሎ ገንዘቤን ቶሎ!

–/ስልኩ ጆሮው ላይ ሲዘጋበት ይራገማል።/– ይዝጋህ!!

–/ዳንኪራ ቡድን የኮንሶ ስልት እየደነከረ ይገባል።/–

ኮንሶ:–ባፍንጫዬ ይውጣ!

ግፍ

አክፍእንትፍ።

ግፍ

አክፍእንትፍ።

ባፍንጫዬ ይውጣ!

–/መብራት ይጠፋል። መብራት ይበራል። ትዕይንት የዘር ነገር ይቀጥላል።/–

ትዕይንት ዘጠኝ

የዘር ነገር

ነጋ :የዘር ነገር ነው ዛሬ፣ ዓለምን የሚያናግር። የሰምና የጉሣ ነገር። የሰላምና የፍቅር ጉሣ የሌለብን ደም የለም። የዘር ሀብታም ነን። የጉሣ ሁሉ። እደዱ እናቴ በእናቷ አያት ትገራይ ነን።...ወሎዬ።.....ከወልዲያ ተሰዳ ወሎ ቦረና በተውጠ ጊዜ በተገሪነት አባቴን አገኘችው። እኔን በሆዷ ይዛ እንደገና ከቦረን በርሬ ደሴ ዙሪያ ኡርጊላ ከልል በስደት ወለደችኝ። የአባቷ ወግ እንዳይቀር፣ ራያ ቆቦና ዋልዲደን ውቃቢ አምላክ በንዝት ቃኗ ጠርታ፣ በዱበርቲና በግቃ-ባላ ስሜን ሰሙ-ንጉሤ። አሰየመችኝ። "ናጋ" አለችኝ። ሰላም ግለት ነው "ናጋ"። ጤና ግለት ነው"ናጋ"። "ናጋ"

ከደቡብ ምድር ሰሜን ቦረና በተውጠ ዘመን ዘምቶ የነበረ ሰው፣ አሥር አለቃ ዲግ ባሪሣ እሚባል፣ ነበር አንድ ያባቴ ጓደኛ። አሥር አለቃ ዲግ ባሪሣ ያኔ ሚሊሺያ፣በአቡጊዳ ቴአትር ጊዜ ከአባቴ ጋራ ተዋናይ የነበረ፣ ከደቡብ ምድር ሰሜን ቦረና ዘምቶ፣ ጓደኞች ሆነው ነበር። በስደት ሠፈር።

እደዱ እናቴ ናት ታሪኩን ያስጠናችኝ። ሰሙ በዘበት ዲግ ባሪሣ ያ ገባር ጉጂ በመባል ብቻ፣ ብዙ ጊዜ ሹመት ይዘለል ነበር። በጀብድ የሚበልጣቸው ጓደኞቹ በሙሉ፣ እስከ ሙሉ መቶ አለቅነት ማዕረግ ሲደርሱ፣ እሱ፣ አሥር አለቃ ዲግ ባሪሣ እንደተባለ ቀረ። ባለበት ዛገ። ታድያን አንድ ቀን ይህን መረር ችግሩን ለአባቴ አወያየው። ያንጀቱን ቁስል ዘረገፈለት።.....የስም ነገር ነው ዛሬ ዓለምን እሚያናግር አየሽው እቴ ገደይ።-ታዲያን አባቴም ለአሥር አለቃ ዲግ ባሪሳ፣ የሰሙን ችግር የልቡን ምክር መለሰና መከረው።...የክርስትና ስምህ እኮ ወልደገብርኤል ነው አለው። የገብርኤል ልጅ። ዲግን ለጊዜው ትተህ ወልደገብርኤል ተብለህ እንደገና ተመዘገብ አለው። ባሪሣ ደሞ ንጋት ግለት ነው። አሥር አለቃ ወልደገብርኤል ንጋቱ ብለህ ተመዘገብ፤ ከጅብዱ ብልጫህ ጋር አይዘህ ያዋጣል አለው። ግመልከቻውን ፃፈና ሰጠው። ቃለ-ምሥክር ጥራ በሚሉህ ጊዜ እኔኑ ጥራኝ አለው።.....አንድ መንፈቅ አልሞላም፤በተከታታይ ሹመት ምክትል መቶ አለቃ ወልደገብርኤል ንጋቱ ዕድገት አደገ።..... ታድያን ያን ቀን የምሥራቹን ጓደኞቹን ጋበዘ። አባቴን ጭምር። ብዙ መጠጥ ጠጡ። ምክትል መቶ አለቃ አስቀድሞ ሰከረ። ተናገረ። ያንጀቱን ቁስል ዳግመኛ ዘረገፈ። አየህ መምህር ወዳጄ ሰሙ-ንጉሥ፣ አለ። አባት እናቴ ያወጡልኝን ዲግን የጉጂ ጉሣ የክብር ስሜን፣ እንደአንኮላ ማንጠልጠያ አስበጥሼ፣ ወልደገብርኤል የሚባል አዲስ ማንጠልጠያ አንጠልጥዬ፣ ምክትል መቶ አለቃ እድገት ነው ውርደት ወረድኩ። አፈርኩ። እንዴት ዕድሜዬን ሙሉ ዲግ ባሪሣ በመባል ስሜ ስጠየቅበት፣ በክፉዎች ባህል ስረገምበት፣ በስሜ ምክንያት ብቻ ተጠርጣሪ ዜግነት፣አንድም ቀን እኔ ጠያቂ ሳልሆን ሁሌም ተጠያቂነት፣ ተመርማሪነት ይፈረድብኝ? ምነው! እንዴት ዓይነቱን ዕድፋም ባህል ነው እድሜ ልክ የሰም አሥር የፈረደብኝ ወንድሜ ሰሙ ንጉሥ?! እስቲ ንገረኝ!.....አሁን ደቡብ ጉጂ ወርጄ፣ ወደ ቀዬዬ ተመልሼ፣ አብሬ አፈር ፈጭቼ ያደኳቸው ጓደኞቼ ፊት፣ ምክትል መቶ አለቃ ወልደገብርኤል ሃኝ ወንድሞቼ ሳሙኝ ብል፣ እውነትስ በልባቸው የለቅሶልኛል፣ ይጠየፉኛል ወይስ ይስሙኛል?!.....ምኔ ነው ወልደገብርኤል ባባትህ አምላክ በቀዬህ አድባር፣ ወንድሜ ሰሙ ንጉሥ፣ ባክህ ንገረኝ! ምኔ ነው ወልደገውርኤል አለና ጮኽ!አባቴ እግር ሥር ተንበርክክ!አለቀሰ!....አባቴም አብሮት ተንበርክኮ አንገቱን እያቀፈ፣ አሁን እድገትህን ካገኘህ ነገ እኮ ተመልሰህ ምክትል መቶ አለቃ ዲግ ባሪሳ ልትባል ትችላለህ፣ በቃህ አታልቅስ ቢለው፣ ከተንበረከክበት ድንገት እንደጥይት ብድግ አለ። እጅግ በቀዘዘ ተግሣፅ አዘል ቃል፣ እነሱ እኮ የሾሙት ወልደገብርኤል ንጋቱን እንጂ ፈጽሞ ዲግ ባሪሣን እኮ አደለም! እንካ ይኸን ያንኮላ ማንጠልጠያቸውን መልሰህ ጣልላቸው፣-/ከኩቱ ላይ ኮክቡን ይበጭቃል፤ ወደ መሬት ይወረውራል/- ያውልህ ብሎ ወረወረለት። እኔ ወልደገብርኤል አደለሁም! ምኔነው ወልደገብርኤል!? አሥር አለቃ ዲግ ባሪሣ ተብዬ ብቀር የበለጠ ክብሬ ነው አለው!-/ፋታ/-አባቴም ሰሙ ንጉሥ በፀፀት ልሣን እውነትክን ነው አለና፣ ምክትል መቶ አለቃ ማዕረግ ማንጠልጠያውን፣ከግስታወሻ ጋር መልሶ አስረከባቸው። ከዚያች ዕለት ጀምሮ ዲግ ባሪሣም፣ ማንጠልጠያውን ጥሎ፣ እንዲህ እንደኛ ለታጋይነት ተመዘገበ። የስም ነገር ነው ዛሬ ዓለምን የሚያናግር። አየሽው እቴ ገደይ።-/ረዥም ፋታ። ሀዘን ቅሬታ ልሣን/- እኔም እንደ ዲግ ባሪሣ ዛሬ የልቤን ቁስል ላንቺ ብቻ ነው የምናዘዘው። -/ኡኡታ/- "ናጋ"ነኝ እንጂ ነጋ አደለሁም!!-/ፋታ። ቀዛዝ ትካዜ ልሣን/- አየሽው እቴ ገደይ። እንደበታቸው "ናጋ"ግለት አይችልበትም። ምላሳቸውን ያደናቅፋቸዋል። "ናጋ" ግለት ሰላም ነው። በንፍገት ልቦናቸው "ናጋ" ግለት አይችሉበትም። ይጠናወታቸዋል።.....ያንጀቴን ቁስል ያንጀቴን ቁስለት ፊት ለፊትሽ አንጥፌ፣ ይኸው እባክሽ ላሳይሽ እቴ ገደይ። ዕድሜዬን ሙሉ ትክክለኛ ስሜን ሰምቼ አላውቅም። ነጋ ነው እንጂ "ናጋ" የሚለኝ የለም። .....ባክሽ የዛሬን እንካን አንድ አንቺ ብቻ ስሜን አሰሚኝ። ታጋዩ "ናጋ" በይኝ። እባክሽ እቴ ገደይ።

-/ሁለት እጆቿን በሁለት እጆ ይዞ ተንበርክኮ ይለምናል።/-

ገደይ -/ከረዥም ፋታ በኋላ በጥሞና ልሣን/- ለምንድነው ሁልጊዜ እቴ እምትለኝ?

ገደይ -/ሁለት እጆቹን ይዛ ከተንበረከከበት ታነሳዋለች።/-ለምንድነው ሁልጊዜ እቴ እምትለኝ?

ነጋ እቴ አበባሽ እቴ አበባዬ የሚለውን፣ ሀዘን የተደባለቀበት የአዲስ ዘመን ምሥራች ዘፈን ግዜም ታውቂበት የለ?

ገደይ -/ታዜግለች፣/-
"እቴ አበባሽ ስትለኝ ከርማ
ጥላኝ ሄደች በሐምሌ ዉለግ።"

ነጋ ጥላኝ ሄደች። ትታኝ ሄደች። በቀውጢ ዉለግ ቀን አራሷን ልጃችንን እኔን ወንዱን እንደ ሴት አሳዘለቺኝና፣ እንዲህ እንዳንቺ እቴ የምላት የነበረችው ሚስቴ፣ ጥላኝ ሄደች! ልጅህን እዘል። እኔ የእናት አገር ጥሪ አለብኝ!እንካ ብላኝ በጉርፍ ጭቃ በሐምሌ ዉለግ፣ ጥላኝ ሄደች።

-/ሁለቱም/ -/በጎብር እያዜሙ እጅ ለእጅ ተያይዘው ይወጣሉ። ቢ.አራጋው ሳያዩት፣ ከኋላ ቸው ይገባል።/

"እቴ አበባሽ ስትለኝ ከርማ
ጥላኝ ሄደች በሐምሌ ዉለግ።"

ቢ.አራጋው -/ከወጡ በኋላ መድረክ መካከል ቆሞ በከፍተኛ ቁጣ ይጣራል። ከሽንጡ በላይ ራቂቱን ነው/-

ዳንኪረኛ ገደይ! ዳንኪረኛ ገደይ!! ነይ!!!

-/ገደይ በድንጋጤ ሹክክ ብላ ትገባለች። ቢ.አራጋው በምሬት ይገሥፃታል።/-
የወንድሜን ልጅ አንድዬን ታጋይ ነጋ ሰሙ ንጉሤን፣ ከኔ ከወንድሙ ደብቀሽ አሁን በፍቅር ልትለክፊው ያሰፈሰፍሽው፤-ከሁሉ በፊት የሽርሙጣ ቤት አስተነባሪነትሽን ለምን ደበቅሽው?! መሠሪ ወጥመድሽን ፍቅር ነው ብለሽ ሳታጠምጂበት በፊት፣ ለምን አባሽ እኮ ነው ሽርሙጣነትሽን ያልገለጥሽለት?! ለምን አባሽ?!....አስቀድሜ እኮ የወንድምህ የቢ.አራጋው የግል ቅምጥ ሴተኛ አዳሪ ውሽማው ነበርኩ ለምን አላልሽውም ነበረ፣ አንድዬን ወንድምዬን በፍቅርሽ መተት ከመተብተብሽ በፊት?! ለምን!!?

-/ገደይ እየተርበተበተች መልስ ልትሰጥ ስትቃጣ ከመቅፅበት በሰደፍ ነጭቶ በደረቷ ይዘር ራታል። ጠመንጃውን አቀባብሎ ጀርባዋ ላይ ይቀመጥባታል። እንደመድፈርም ይቃጣባታል። በመሬር ይዝትባታል።/-

እስቲ አባሽ ሁለተኛ አንድዬን ወንድምዬን ፍቅር ታስይዢውና!? እስቲ አባሽ ሁለተኛ!?

-/ ጠመንጃውን እንዳቀባበለባት ድንገት ብድግ ይላል። ውልቅ ብሎ ይወጣል። ገደ ይ በታላቅ ሰቀቀን የልቅሶ ዋይታ መድረኩን ታድበለቀልቀዋለች። ረጅም ፀጥታ። ዳንኪራ ቡድን"አዩ እቴ አበባዬን"የአዲስ ዘመን ጭፈራ እየደነከረ ይገባል።/-

አዩ!"እቴ አበባዬ

አዩዩ!አዩዩ!አዩ!

አዩዩ፣ እቴ አበባዬ

እቴን-እቴን-እቴን-እቴን

እሽረረረረ

አዩ እቴ አበባዬ

-/ዳንኪረኞቹ ሲወጡ ገደይ እንደገና፣ "አይ!!" በሚል ዋይታ አዳራሹን ታድበለቀልቀዋ ለች። መብራት ይጨልማል። ትዕይንት <u>አዩዩ ምህላ</u> ይቀጥላል።/-



ロシアリ ナンシナ ロキナ

ትዕይንት አሥራ አንድ

ልምድ

ቢ.አራጋው –/ስልክ ይዟል። ከሽንጡ በላይ ራቁቱን ነው። ሌንሣን ዳንኪራ ያለማምዳል።/–
ከዳሌሽ ሽቅብ ሽቅብ ሽቅብ! ከአንገትሽ ቁልቁል! ቁል ቁል ቁል ቁል ቁል ቁል ቁል!
ሐረርጌ ኦሮሞ ቆቱ አንገት አሽከርክሪት ዛር፣ ሽጉዱ እኮ ነው ያልኩሽ! ኩርርርር!
ዳንኪረኛ ሌንሣ ለምን አትሰሚኝም?! እንደወንዝ ሽከርክሪት የአንገት እንዝርትነት ነው
የሽንጡ ምሥጢሩ፣ እንደሰንጋ ፈረስ ሜዳ ሙሉ ማናፈር እኮ አይደለም! ቀፋፊ ዳንኪራሽን
አትመናቀሪብኝ። ፀረ ቱሪስት ዳንኪራ። የግታ ክበብ የቱሪስት መስህብ ቤቴን ያስዘጋብኛል
ያንቺ ሰንጋ ፈረስ ዳንኪራ። ኋላ ቀን ተጠንቀቂ ወይዘሪት ሌንሣ!.....አንተን አደለም
ሀሎ ዳንኪረኛይቱን ነው፣ ምን ነካህ አንተ ደሞ?!.....ሀሎ!.....ሽቅብ አልኩሽ ኩዳ
ሌሽ ሽቅብ! እንደጉሽ ጥጃ በጥፍራም ጥፍርሽ ሰላማዊውን ምድር በእልክ አትጉልድሬ! አጥፍ
ዘርጋ ነው አጥፍ ዘርጋ ከሽንጥሽ፣ ዳሩ ሽንጥ እሚባል ቅርፅ ከተም አልፈጠረብሽ እንጂ!.
...ሀሎ!አንተን አደለም አልኩህ ዳንኪረኛይቱን ነው!–/ፋታ/–ሀሎ!....ምን ሕዝብ?
ዘራፊ ሕዝብ?!ዘራፍ ዘራፍ ሲል አድጉ ቀኑ ሲያመቸው ላይዘርፍ ናሯል ኋላ! የአባት ባህል
እኮ ነው ምን አርግ ነው እምትለው?!.....አምን ዘርፎ መብላቱ!! አምን ያባቱ!!..
ሀሎ እሱንማ ነግሬሀለሁ አልነገርኩህም እንዴ?! ወጣሁ እኮ ከኢትሀረቅ። ኢትግግረቅ ገብ
ቼ! ነግሬሀለሁ እኮ። ኢትግግረቅ ቅንብር ግንባር ከገባሁ ቆየሁ ብዬ?!...አምን ከግን
ባር ወደ ግንባር!....ተው ባክህ አትምከረኝ ይልቅ እኔ ልምከርህ! ካንተ ይልቅ
እኔ ነገር አዞራለኋ። አላምጣለሁ። እንተ ነገር አታዞርማ! እታላምጥም። "ያላዞረ ሲዞር
አደረ"ነዋ። እንዲህ እንዳንተ።....ለኔ ብለህ እንደሆን ዕድሜህን ሙሉ ስትዞር አለቅ።
አምን አለቅ። አትምከረኝ። አባክህ ይልቅ እኔ ልምከርህ! ከግንባር ወደ ግንባር መጥ
ለቅ ነው ልክ እንደ ጀምበር! ሲመሽ በምዕራብ መጥለቅ፣ ሲነጋ ደሞ ምሥራቅ መጥለቅለቅ!
ምን አልክ?!....በታሽ ባለሽበት ቆይ፣ ዳኪረኛዋ ሌንሣ አትመናቀሪብኝ! ምን
አልክ?!....የቀሩትሳ?የቀሩትሳ ድርጅቶች?! የቀሩትማ ያው የቀሩ
ናቸው!...ሽ?!.....የቀሩት ናቸው አያልክ ከግንባር ግንባር አንዴ ስትጠልቅ አንዴ
ስትወልቅ ጥይት በግንባርህ እንዳይጠልቅ?!....ያማ የመጠሪያው ቀን ሲደርስ፣ ና ብሎ
እንድቱ በጠራበት ቀን፣ አልመጣም ብሎ የቀረ ግንን አይተሀል? ከላይ ተቆርጦ ጥሬው
ሲመጣ፣ ሁላችንም ሂያጆች ነን ባክህ!....ተው? ተው አትበለኝ ባክህ ይልቅ አንተ ራስህ
ተው!!.....የምን ምሥጢር?! የማን ምሥጢር?!.....ሁለተኛ ምሥጢርክን ለኔ
እንዳትናገረኝ!ነግሬሀለሁ! ትላንት የነገርከኝም ሆዴን እንደጉረበጠኝ ነው! እኔ ያንተ
ምስጢር ማጉሪያ ስልቻህ እደለሁም! ትይዝ እንደሆነ ምሥጢርህን እዚያው ለራስህ ያዘው!
አለበለዚያ እኔ ቢ.አራጋው፣ ወዲያ አውጥቼ ነው ጉድክን በሜዳ
እምዘረግፍልህ!...ምን?!...ስለኔ አደለም ስላንተው ምስጢር ስላንተው ጉድ ነው?
እኔ ቢ.አራጋው ደሞ ምን ጉድ አለብኝ አንተ?! ምን ጉድ አለብኝ!....ፋይል ተገኝቶብ
ሀል?! የቤት ወራሽነትህ ያጠራጥራል?! ትክክለኛው ወላጅ አባትህ ገና አልተረጋገጠም?!
–/ዳንኪረኛ ሌንሣ ከነበረችበት አቋቋም እንገቷን ወደ ቢ.አራጋው በመደነት ታዞራለች።
ስልኩን ትቶ እየተንደረደረ ወደእሷ ይሄድና እንገቷን እንደነበረ ይመልሰዋል። በታላቅ
ቁጣ/–በነበርሽበት ቆይ ብያለሁ ዳንኪረኛዋ ሌንሣ! ባለሽበት ቀጥ በይ!! –/ወደስልኩ
ተመልሶ በእልህ ልሣን/– እንዴት እባክህ እንዴት እኮ በል?!....–/አጭር ፋታ/–..
...ታድያን ወላጅ አባትህ ሊኖር ቢያንስ ባለጋራሽ ጣልያን ነው፣ ያለቺኝ ወላጅ እናቴ
ጌኒ አምበርብር ናት! ስምክን እንደ ወላጅ አባትህ ቢያንስ ብዬ፣ ለማሳደጊያህ ጋራዥ ንብ
ረቱን በጠበታ ከስሼ፣ በሕግ አስጠብቄ፣ አስይዤ፣ አስሸው ተካፍዬ፣ ለኔ ቪላ ገዝቼ ይህ
ን ላንተ አወረስኩህ ያለችኝ እሷ! ጌኒ!ምነው ታድያን ቆዳዬ፣ ፈረንጅ ከወለደኝ፣ ትንሽ
የከልስ ቅላት አልፈነጠቀብኝም፣ ያው እንዳበሻ ቆዳ ድፍን ቱባዬን እንደጠየምኩ ቀረሁ፣
ምነው ጌንዬ ብላት፣ እኔን አትዉቅሮቀኝ፣ ጠበታዬን ጠይቀው፣እሱ ብቻ ነው ነገር
እሚያውቀው፣ ብላ ያሾፈቺብኝ እሷ! ጌኒ! ዛሬ ታድያን እናንተ፣ፋይል ተገኝቶብህል
እያላችሁ፣ ይልቅ እውነትኛው አባትህ፣ የገዛ እናትህ የነፍስ አባቷ፣ የኔታ ገራ ጌታ፣
ሆነው ተገኙ የምትሉኝ ጉድ፣ የሷ ነው እንጂ የኔ ጉድ አደል! –/ሌንሣ ተገርማ ወደ እሱ
ትዞራለች። ተንደርድሮ ሄዶ እንገቷን ወደ ነበረችበት ይመልሳታል። በስልኩ ይቀጥላል።/–
ታድያን እናቴ ጌኒ በቀባዥረች እንዴት ውርሴን ልጣ እኔ?! ጠበታውም ከሆነ ተይዞ
ይመርመርልኝ! ምሥክር ብትፈልጉም እነ የኔታ ገራ ጌታ ጋዱንም፣ አምላ አለቃ ጣሴንም፣
የከሰረውን ጣልያን ሲኖር ቢያንስ፣ ጥሩና ጠይቋቸው!ሰነቱም እዚህ ከተማ አውራ ጉዳና
ለማኞች ናቸው ዛሬ! አምላ አለቃ ጣሴ፣ የቀኝ እጁን ተቆርጦ፣ ሁለት ዓይኑን ታውሮ፣
ቀበሌአችሁ ደጅ ነው የሚለምነው፣ የትም አያመልጣችሁ።.....ግደሪያው?! ግደሪያውማ
እዚሁ እኔው ጓሮ ነው። በገዛ ጓሮው ማን ይከለክለዋል!ጥሩና አስጠይቋቸው! ጠበታውም
ከሆነ ተይዞ ይመርመርልኝ! እናቴ ጌኒ በቀባዥረች፣ እንዴት ውርሴን ልጣ እኔ?!
–/ስልኩን በቁጣ ይዘጋል። ወደ ሌንሣ ይሄዳል። በከፍተኛ ብስጭት ልሣን፣/–ምከሪኝ
እንጂ ምንድነው ኩሪፊያው?! አባትህ አልታወቀም፣ ፋይል ተከፍቶብህል፣ ወራሽነትህ

ያጠራጥራል፣ ነው እኮ እሚሉኝ! ምክሪኝ እንጂ ምንድነው ኩርፊያው?!

ሊንሣ —/በነብረችበት የዳንኪራ ቅርፅ ሳትነቃነቅ በቁጭት ልሣን፤/— ካንተ ጋር መኖር ላስቻለኝ አምላክ ክብር ምሥጋና ይግባው!

በ.አራጋው ሰላም አጣሁ እኮ ነው እምልሽ ምንድነው ኩርፊያው?

ሊንሣ —/ባለችበት እንዳለች በበለጠ ቁጭት ልሣን/— ካንተ ጋር መኖር ላስቻለኝ አምላክ ክብር ምሥጋና ይግባው!! ሰላም ትላለህ እንጂ ሁለታችሁም ያው አንድ ናችሁ። "ሰላምን አታገኙም። ሰላም በውስጣችሁ የለችምና።"

ቢ.አራጋው በቃሽ ይሽን ኢንጪኛ ምላስሽን ተይ! ዳንኪረኛዋ ሊንሣ ልምምዱን ብቻ ቀጥዪ! ቀጥዪ!! —/ትቀጥላለች/— ከዳሌሽ ሽቅብ፣ ሽቅብ! ከአንገትሽ ቁልቁል! ቁል ቁል ቁል ቁል ቁል ቁል! —/ተፈናጥሮ ይወጣል። ሊንሣ ብቻዋን እየተለማመደች መብራት ይጠፋል። ከዘጠኝ ወር በኋላ። መብራት ይበራል። ትዕይንት ሴት ልጅ ይቀጥላል።/—

ትዕይንት አሥራ ሁለት

ሴት ልጅ

-/ከዘጠኝ ወር በኋላ ሊንሣ በልምምድ ትዕይንት ላይ በነበረችበት ሥፍራ እንደተንከላወሰች ደክሟት እፎይ ብላለች። ነጋ ጉኗ ተቀምጦ ያዳምጣታል። ጠመንጃውን ተቀብላ አፈ-ሙዙ ውስጥ ጢና አዳምና ቂጢግ ትተከልበታለች። ረጅም ፋታ።/-

ሊንሣ — ጠመንጃህ ጢና አዳም ያውቃል?

ነጋ — ጠመንጃ ነፍስ የለውም።

ሊንሣ — ሰው ብቻ ነው ነፍስ ያለው። ራሱ ነፍስ ያለው አዲስ ነፍስ የሚዘራ።

ነጋ — ምን ማለት ፈልገሽ ነው?

ሊንሣ — አየህ ታጋዩ ነጋ። ዘለዓለም ዓለም የሴት ልጅ ታሪክ ዘጠኝ ወር ሞላት መባል ብቻ ነው። ....ፍቅረኛህ አዶዬ ግደይ፣ ከወንድምህ ከአዘጋጅ ቢ.አራጋው፣ እንደምታውቀው ሴትነቷን ተደፍራ ተገዳ ከፀነሰች፣ ይኸው ዘጠኝ ወር ሞላት። ዛሬ በጠዋት ሴት ልጅ ተገላገለች። አዲስ ነፍስ።

ነጋ — -/ንፍገት አዘል አልሀ ልሣን/- እኔ ታድያን ምን ላርጋት?! እኔ ታድያን ምን አውቅላታለሁ?!

ሊንሣ — -/ፋታ። ቀዛዝ ኮናኝ ልሣን/- አምን አታውቅም።....የኛ ወንዶች፣ ስለኛ ሴቶች፣ ዘለዓለም ዓለም፣ ምንም አታውቁም። ባህላችሁ ነው። እኛም ሴቶቹ የሚጠቀሙበንን እንጂ የሚጠቅሙንን መጥቀም አይፈቀድልንም። ባህላችን ነው።

ነጋ — -/በባሰ እልሀ/- እኔ አላውቅም!

ሊንሣ — -/ፋታ። በበለጠ ኮናኝ ልሣን/- አምን አታውቅም።-/ፋታ/- ዘለዓለም ዓለም ጭፍን ጭልም ድፍን አርጋችሁ አምን አታውቁም። የኛ ወንዶች። -/ፋታ/- አሁን አንተ ስለኔ እኔነት፣ ምን እምታውቀው አለ?....ድቅድቅ ጨለማ፣ እጅግ እምቅ ብችኛ እኮ ነው፣ በዚች ባበሻ ምድር የሴት ልጅ ልቧ። እምቅ ብቸኛ። ድበቅ ጭልም ስሜታን፣ በንቃተ ባህል ውስብስ ሜካ ገብቶ፣ ማንም አያውቅላትም። በነገር ቀደም ሁሉ ያውቅባታል፣ በነገር ቀደም ሁሉ ይፈርድባታል፣ እንጂ ማን ያውቅላታል?!....አንተ የኔን የሴት ልጅ ምጭት የት ታውቀዋለህ? ያበሻ ወንዶች እኮ በኛ በሴቶች ዘለዓለም ዓለም ታውቁብናላችሁ በስተቀር ከቶም አታውቁልንም። እኛ በናንተ መፈቀድ ወይም መመረጥ በቀር የኛ ምርጫ የት ይጠየቃል። እኛ ምጭታችንን፣ እኛ ዕድላችንን፣ እኛ ፈቃዳችንን፣ እኛ ስሜታችንን በውስጣችን ፍግም አድርገን ቀጭተን፣ ለሚጠቅምብን ወንድ እንደዕቃ መቅረቡን ነው፣ ከኛ አልፈን ተርፈን ለሌሎች ለማስተማር የፈረዳችሁብን ባህል። -/ፋታ። ተረት ልሣን/-የነፍስ አባቷ በግድ እናቴን አንቀው ደፈሯትና፣ እሷ በየዋህነት ጉዱን ላባቴ ብትናገር፣ አባቴ እሷኑ ደበደበና ፈነከተና፣ ፈታት። ከቤቷ አባረራት።....ይኸ ብቻ ነው፣ የኛ ያበሻ እናቶች፣ የሕይወት ታሪክ።...አዶዬ ግደይን፣ ወንድምህ ቢ.አራጋው፣ ባስገደዳት፣ በደፈራት፣ ባዋረዳት፣ ባስፀነሳት፣ አንተ ለምንድነው እሷን የምትዘጋት?! የምታኮርፋት?! የምታሳጣት?! ለምንድነው በደሏን የማታውቅላት?!

ነጋ — -/በባሰ እልሀ ልሣን/- እኔ አላውቅም!

ሊንሣ — -/ረጅም ፋታ። እጅግ በቀዘዘ ኮናኝ ልሣን/- አምን አታውቅም። የሴትን ልጅ ታሪክ አታውቅም። የራስክን ሰሚት በቀር፣ የራስክን ፈቃድ፣ የራስክን ተስፋ የነገ ምጭትና ሕልም በስተቀር፣ ያበሻን ሴት ልጅ፣ ያበሻን እናት፣ ተስፋና ሰሚት፣ ምጭትና ሕልም፣ አምን አታውቅም! አምን አታውቅ!!

-/ትወጣለች። መብራት ይጨልማል። ነጥብ መብራት ነጋን ሲከብበው ሕልም ሥነ-ግጥም ይዋ ነያል።/-

ነጋ — ምን ይመስላል የነገው ቀን፣ በእንቅልፍ ራዕይ የሚታየው?

ስዎች ሕልማችሁ ምንድነው?

ፍቅር በእልህ ላይገታ

ሕልም በቂም ላይፈታ

ስሜት ናሮን ስሜት ግንድ

ፈቃድ ናሮን ፈቃድ ግንድ

መድፈር ግዋረድ ግስገደድ

ያውቅበታል ያበሻ ወንድ.....

ሕልም ግን አይገደብም

ለግንም ሆነ በምንም።.....

እና ሕልማችንን እንይ

ከፍካሬ ኢየሱስ ይልቅ፣ ብሩህ ተስፋ ብሩህ ራዕይ።

ሰላም እንዲቀናን ከቀውስ

ከእኩይ ሀልፈትም አዲስ ነፍስ

ሕዝቦች፣ምንድነው ሕልማችን?

ዘለዓለም ዓለማችንን፣ ለጠመንጃ እንሰግዳለን?

ወይስ ጠመንጃውን ሰብረን

አቅልጠን ዳግም ቀጥቅጠን

ግረሻ እናደርገዋለን?.....

ሕልማችሁን ገለጡልኝ፣ እንጂ አናልምም አትበሉኝ፣

ሕልም አይቀርም፣ አታግልሉኝ.....

ሰው የሚባል ግንም፣ እንድም

የማያልም አይገኝም።

ቅዠት ነው ብትሉኝ እንኳን፣ ቅዠትም ቁንጋፍ ሕልም ነው

ለሊት በእንቅልፋችን ወድቀን

ቃዠቶ ለሚተረጉመው።.....

በሕልማችን የሚታየን

ብርሃን ነው ወይስ ዉለማ? ተስፋ ነው ወይስ መቀመቅ

እርይታ ነው ወይ መጪነት?

ድቅድቅ ነው ወይ አዲስ ዓለም?

ምንድነው የሕልማችን ቀለም?!

ምሥራች ነው ወይስ እክል?

ሕልማችን እንድሁ አይለቀን፣ እናልምህ ግለት አንችል፣
ብንፈልግም ባንፈልግም፣ ደክመን በግድ ለባታችን
ሁላችን፣ እያንዳንዳችን
አሸልበን በእንቅልፍችን
ብንወድም ባንወድም፣ ቦግ ይልብናል ሕልማችን!.....
ሕዝብ ሆይ ሕልምህ ምንድነው?
ነገ ላንተ የሚታየው?.....
በሕዝባዊነት ፈቃድህ
በእኩልነት ተቻችሎ፣ አብሮ የመኖር ምኞትህ
ምን መስሎ ነው የሚታይህ?.....
ቀን ውሎ በእንቅልፍ ጉዞ፣ ሌሊት ላይቀር መታለሙ
ምንድነው ሕልምህ ትርጉሙ?.....
ሰምች ስሙ፣
ሕዝቦች በጉ ሕልም አልሙ።
ከትውልድ ወደ ትውልድ፣ ዘለዓለም ከምናይ እኩይ
እስቲ ሁላችን በግላጭ፣ የነገን ሰላም ሕልም እንይ።

-/መብራት የጨልማል። ነጮድጓድና መብረቅ ይሰማል። የደበዘዘ መብራት ይበራል። ሦስቱ ጠንቋዮች ያሟርታሉ። ሟርት ዳንኪራ ይገዝፋሉ/-

/ሦስቱም/ -/ጭራቃዊ እልልታ ያስተጋባሉ/- እልልልልልል!!

ግደይ ሕልማቸው ይበጥበጥ ብሏል!

ፉፉ ጠቋር አዟል!
በረኸኛው ገውዝ ነፍሏል!

ሌንጣ ጫን! ጫን ፈረስክን ጫን!
ሕልም አደፍርስ አባ ሰይጣን!

ግደይ ሣጥናኤል ከሲኦል መጥቷል!

ፉፉ ጨለማ-አክናፍ አፉን ከፍቷል!

/ሦስቱም/ -/ጭራቃዊ እልልታ ያስተጋባሉ/-እልልልልልልል!!
-/ጭራቃዊ ሳቅ ያስካካሉ/-

ሌንጣ ቀሊል ልጣን ለኩሽበት!

ግደይ ጥይት ምላስ ለኩሽበት!

ፉፉ መቂናጥ አፍ እንደጅራፍ ለኩሽበት!

ሌንጣ እልከኛ ጥፍር ይግዘዝ!

ግደይ ሰብአዊነቱ ይርከስ!

ፉፉ ይሉኝታቢኑቱ ይርከስ!

ሊንሣ የሰላም ሕልሙ ይልኮስኮስ!

ግደይ ጦስ ጥምቡሳሱ ይበሳበስ!

/ሦስቱም/ ቃል አደፍርስ!
አርከስ!
አፍርስ!

ፉፉ እልቂት ቀስቅስ!

ሊንሣ አድባር ገርስስ!

ግደይ ሣር ቅጠሉን አሸዋ አልብስ!

-/ሦስቱም/ -/መብረቅና ነጐድጓድ ይስተጋባል። አውሎ ነፋስ ይነፍሳል። ጭራቃዊ እልልታና ሣቅ ያስተጋባሉ/- እልልልልልልል!!

-/መብራት ይጨልማል። መብራት ይበራል። ትዕይንት ተመረጥኩ እኮ ይቀጥላል።/-



ታጋይ ነጋ ብሔራዊ ቴለትር አድባር ዋርካ ላይ ለመታሰቢያ እንደተቸነከረ

ትዕይንት አሥራ ሦስት

ተመረጎኩ እኮ

ቢ.አራጋው —/ስልክ ይዟል። ጀለቢያና ፎጣ ጠምጥሟል። ቆብ አጥልቋል። ጫት ይትግል።/— አላነሱልኝም?! ስልኩን አላነሱልኝም?! እሱ ካላነሳልሽ አንቺ አንሺለታ! አንቺ ከፍ አር ጊለታ! ከፍ አድርጊና ባፋ አጉርሺሊታ! ሀሎ!!.....አነሳኸው እንዴ? ጉሽ እንኳን አነ ሳኸው።.....ማነህ?! እኔግ ወንድምህ፣ የልብህ! ስልክ አስነስቼ ባፍህ የማስጉርስህ፣ አራጋው ነኛ!.....እሱን ተውና ይልቅስ ስግ!....ተመረጥኩ እኮ! መረጠኝ እኮ! ወረዳ ህዝቤ መረጠኝ እኮ! ልክ እንዳሰስኩት እንደተለምኩት እንደጠበቅኩት ወረዳ ሕዝቤ የልቤን የሚያውቅልኝ የልቤ ሥር ትርታው መረጠኝ እኮ! ሕዝቤ! ደግሞ ደጋግሞ ምርጥ አረገኝ እኮ!ሀሎ! ምሥር ብላ! —/በምሥጋና መሬት ይስግል። ይነሳል/— ምሥር ብላ! ሀሎ!..... ገንዘብክንላ?! አሁን ገንዘብን ምን ያስነሳህል?! እሺ ይቆይ አንተው ጋ! ትንሽ ይቆይ አንተው ጋ!.....ግ?! ታጋዩ ነጋ? ታጋይ ወንድሜ?—/ቀዛዝ ልግን/— አዎን ትንሽ ተቀይሞኛል።—/ቁጡ ልግን/— በዚያች ባንዲት መናኛ የሌሊት ዳንኪረኛ፣ በዚያች በእንከፍ የሌት ወፍ፣ በዚያች በሙሬ ካፍ የወደቀች ጥሬ፣ ታጋይ ወንድሜ ከሚታዘበኝ ከሚቀየመኝ፣ ያውልህ ወዲያ መልስና ውሰዳት፣ ከመጢፍም አልቆጥራት፣ውሰዳት ከነልጇ አልኩት! ራሴ እንዳስተዋወቅኩት፣ መለስኩና ሰጠሁት !ያው መለ ስኩልህ፣ ውሰዳት አልኩት!....ጥያቄ!? ምርጫውን አስመልክቶ የተነሳብህ ሞራል ጎከ ጥያቄ?! እኮ ግን ላይ!? እኔው ላይ?!.....ምቀኛ ነዋ፣ ከቶ ምቀኛ መች ይታጣል?! ምቀኛ አታሳጣኝ ብለን ስንፀልይ አድገን፣ ከቶ ምቀኛ መች ይታጣል?!.....ናፅራዊ እኮ ነን። የነጠርን ዘር። እንደወርቅ ተፈትነን የነጠርን። ምቀኛ እሚበዛብን፣ ግንም የሚቀናብን እንጂ በግንም የግንቀና። ከቶ በኛ ላይ ምቀኛ መች ይጠፋል?!—/ነጋ ይገባል። ቢ.አረጋው ስልኩን ይደረግመዋል። ይቁነጠነጣል። ረጅም ፀጥታ። በቀዛዝ ልግን/—ተመረጥኩ እኮ። ወረዳ ሕዝቤ ደግሞ ደጋግሞ እንደገና መረጠኝ እኮ።.....የምሥራች በለኛ፣ ታጋይ ወንድሜ።

ነጋ ሹመትም ሆነ ምርጫ፣ ለኛ ለአበሻ፣ እንደጓያ ንፍሮ ነው። የአጥንት አንጓ ስብራት። ተሾምክ ባሉት ግግሰት እንኳን አነጋገሩ አረማመዱ ይሽመደመዳል።

ቢ.አራጋው እኔ አልተሸመደመድኩም። እንደበቴም ሆነ አቋሜ፣ሁልጊዜም አንድ ርቱዕ ነው።

ነጋ ለምን ሁልጊዜ ከሰው መካከል መመረጥ ያጓጓህል?

ቢ.አራጋው እኔ ከማን አንሳለሁ?.....ይልቅስ አንተ፣ ዛሬ በየትኛው ጉንህ ነው የተነሳኸው?

ነጋ እንዲያውም አልተኛሁም።

ቢ.አራጋው ታድያን እኔ ብመረጥ ምን ይጐድለኛል? የቀበሌዬ ፣ የወረዳዬ፣ አንጋፋ እኮ ነኝ።

ነጋ እውነትህን ነው ዛሬ፣ ሁሉ አንጋፋ ነው። አንጋፋ መባል እንደፋብሪካ ውጤት ጥሬ ዕ ሆኗል። በዜና ማሠራጫ በዘፈቀደ የሚፈበረክ ጥሬ ዕቃ ውጤት።.....እውነትህን ነው፣ አንተስ ከማን ታንሳለህ?

ቢ.አራጋው —/ቁጣ/—እኔ ምርጥ ነኝ ህዝቤ የመረጠኝ!! በዘፈቀደ የተፈበረኩ ጥሬ ዕቃ ውጤት አደለሁም!!

ነጋ —/ቀዛዝ ሽሙጥ/— አሁንም እውነትህን ነው አንተ ከሁሉም ትበልጣለህ። ከምርጠችም ምርጥ ከአንጋፋም አንጋፋ ነህ።—/አጭር ፋታ። የታመቀ መራር ልግን/— ምክንያቱም አየህ፣ አንተ ከቀላልም ቀላል ነህ። ትንክ ቀሊል ሕዝባዊነት የሌለህ የሕዝቦች ወኪል። የወረዳውን የሕዝብ ጥሪ የሰላም ዋይታ እንደምርታና የጫት ትፋትህ ሕዝብ መድረክ ላይ በድፍረት የምትተፋ የቀላል ቀሊል፣ ሕዝባዊነት የሌለህ የሕዝቦች ወኪል።

ቢ.አራጋው —/ቁጣ/— እኔ ቢ.አራጋው፣አንደበቴም አቋሜም የማይቀየር የማይቀያየር፣ "ኢትዮጵያዊ ቆዳ ውን ነብርም ዥንጉርጉሩን፣ ይለውጠው ዘንድ አይቻለውም" የምባለው አይነት ነኝ። ከቶም የማልለወጥ ሕዝቤ የመረጠኝ፣ ቁርጠኛ ኢትዮጵያዊ።

ነጋ —/በመራር ቁጣ ይገነፍላል/—አንተ ትንክ ነህ! ከድንክም በታች በመንፈስ የደነከይክ እኩይ ትንክ ነህ! ካልጠፋ ወገን፣ የወረዳው ሕዝብ፣ አንተን እንድ ትንክ፣ እንዴት መረ

ጠሀ?! ሕዝብን ማቀጨጭ እንጂ ማሳደግ የት ታውቃለሀ?! አሳድደሀ መቅጨት እንጂ ማሳደግ ልግሥና መቼ ተሠረፀብሀ? እክል የሕዝብ እክል የሰላም እክል! ሀሳዊ መሲህ ግንፍል፣ ከም ድር ማህፀን ድንገት የፈላህ የምፅአት ፍል፣ በሰው ቅርፅ የምትሳብ በላዔ ሰብ ትል!ትን ክ! ራስህ መንፈስ ቀጫጭ ሀሳበ ቁማጭ፣ ሂደተ ቁጫጭ፣ የድንክ በታች እኩይ አያ ሥንዝሬ ደቂቅ ጭራቅ ግልብልብ፣ የሀሊና ሰልብ፣ አንተ ትንክ ነህ!

-/በመራር ቁጣ ተፈናጥሮ ይወጣል። ፋታ።/-

ቢ.አራጋው -/በታላቅ ጨኸት ከኋላው ተከትሎ እየተጣራ/- ለዚያች ለአንዲት መናኛ የለሊት ዳንኪረኛ፣ ለዘያች ለእንከፍ የሌት ወፍ፣ ለዚያች ለሙሬ ካፍ የወደቀች ጥሬ፣ ብለህ አደለም ታጋይ ወንድሜ፣ ሕዝቤ መረጠኝ ስልህ የምሥራች ያላልከኝ?! ለዚያች ለአንዲት መናኛ ብለህ አደ ለም ታጋዩ ነጋ፣ ከአንድዩህ ከደምህ ከወንድምህ ጋር አንጀት ላንጅት መቆራረጥህ?! ኧረ ተው ባክህ!

-/ቢ.አራጋው ከመድረክ ጀርባ ተከትሎት ሲጣራ ድምፁ በሩቅ ተውጦ ይሰማል። ነጋ በመድርክ ዙሪያ ገብቶ ሥነ ግጥም ይሉኝታችንን በላነው ይዋነያል።/-

ነጋ

ጮሌ የምሱን የጮህል
እንደቁራ ኡኡ ይላል።.....
ብሂል በአደባባይ ገድለን
ይሉኝታችንን አውልቀን፣ ጥለን
እራቁታችንን ቆመን፣
ደሞ በኛው ይባስ ብለን ባደባባይ እንጮህለን።.....

-/የቢ.አራጋው ጨኸት ጥሪና ስድብ አልፎ አልፎ ከሩቅ እየጐላ ይደበዝዛል/-
የምወዳትን ከጐኔ፣ ጠልፎ ለክፎ ለእክል ዳርጐ
መናኛ አርጐ፣
መናኛ ናት ይላል ጮሆ፣ እሱ አርክሶ እሱ ፈርዶ!.....

በቀን ጨኸት ያለለከት

ሲመሽ ውርደት

ነው፣ የኛ እውነት!!

የኛ ብሂል!!ሌላው የኛ ክፉ አባባል

መጀመሪያ ክብር ይገድላል፣ እንደገና ስም ይገድላል፣

እንደጅራፍ ድምፅ አፀፋ፣ የገደል ማሚቶ አረሆ

እሱው ገድሎ እሱው ጮሆ።....

ይኸን ጮሆ መረጋገም፣ መላከፍ ቆሌ ለቆሌ

ተው እኔን አይተህ ተቀጣ፣ አለ አሉ ወንድም ሶማሌ!

አባቶቻችንን ረግመን

ልጆታችንን ሽንግለን፣ ለራብ ጥለን ለጦር ጥለን ለሞት ጥለን

እናቶቻችንን ረግጠን፣ አቆሸሽን መናኛ አርገን

መልሰን መናኛ ብለን

እስከመቼ እንጮህለን?!
እስከመቼ!!.....
ጮሌ የምሱን ይጮህል
እሱው ገድሎ እሱው ዞሮ፣ እንደቁራ ኡኡ ይላል።
-/መብራት ይጠፋል። ትዕይንት ቁራ ይቀጥላል።/-

ሌንሣ -/ልቦናዊ መሪም ልሣን/-ሽግግሊዎች?! ሽግግሊዎች ልከሀበት ነበረ እንዴ?

ቢ.አራጋው -/በንፍገት ልሣን/- አንቺን ምን ያገባሻል?! ሽግግሊ ላኩ አልላኩ አንቺን ምን ያገባሻል?!

-/ረጅም ፋታ። ግንግጠጥ ልሣን/-ይልቅ የመጣሽበትን ዉርሺ። ሮጠሽ የመጣሽበትን ጉዳይ ዉርሺ።

ሌንሣ -/ረጅም ፋታ። ተእዝብቷን ውጣ በጥሞና አዘል ልሣን/- አስተራርቀናችኋል። አዶዬ ግደይና እኔ አስተራርቀናችኋል።.....ወንድምህ ቢቱን ላንተ ትቶልህ፣ ሁለቱንም ሕፃናት ደሜ ወገኔ ናቸው ብሎ በግራና ቀኝ ትከሻው አዝሎ፣ ጠመንጃውን አትልጦ ግረሻ ሊያረግ ምሎ፣ ደሴ ዙሪያ ኡርጌሣ እናቱ ቀየ ለመመለስ ወስኗል።.....አስተራርቀናችኋል።

ቢ.አራጋው -/በታላቅ ደስታ ፍልቅልቅ ልሣን/- ፈጽሞ አላምንም! እኔ ይቼን ፈጽሞ አላምንም! -/በምሥጋና መረት ስሞ ይነሳል/-አያረገውም! አያረገውም!! አያረገውም እንጂ ካረገውን፣ እዚያው ደሴ ዙሪያ ኡርጌሣ ወደ እናቱ ጋ ከፈደሉ ጋር ሁለቱንም ሕፃናት አዝሎ፣ ልክ እንደአባቱ። እኔም የቱሪስት መስህብ ሌት ዳንኪራ ክበቤን፣ መሀል አዲስ አበባ፣ያው እንደእናቱ "ሆሆይ!" መዉረር ነዋ! አያረገውም እንጂ ካረገውማ--

ሌንሣ -/በቀዘዘ ትእዝብት ልሳን ታጽርጠዋለች/- ያረገዋል። አስተራርቀናችኋል።

ቢ.አራጋው -/በግንግጠጥ አፀፉ ቁጣ/- ታድያን እንቺን ምን እዚህ ይገትርሻል?!ቶሎ ቤት ተመልሰሽ የሌት ክበብ ዳንኪራ ልምምድሽን አትቀጥይም?! ለምን ጊዜዬን ታባክኛለሽ?! ጊዜ ዶላር ነው ዳንኪረኛዋ ሌንሣ!
-/ወደራሱ ደስታ ፍንደቃ መለስ ብሎ ሆሆይ እያለ ጀርክ ይደንሳል/-ሆሆይ!!

---አየሽ እንዲች እያረግሽ የምሥራች ጀርክ ዳንኪራ ቶሎ ሂደሽ ተለግመጂ ዳንኪረኛይቱ ሌንሣ! --

ሆሆይ!!

--አየሽ፣እንዲህ እንደኔ።--

ከዳሌሽ ሽትብ! ሽትብትብ!

ከሽንጥሽ እጥፍ! እጥፍጥፍ!

እንዲህ እንድኔ!.....

ሆሆሆይ!!

-/ድንገት ይቆማል። ያፈጥጣታል። በንፍገት ልሣን/-ምን ታፈጪብኛለሽ ዳንኪረኛዋ ሌንሣ?!.....-/ትእዛዝ ልሣን/-ሂጂ ተለግመጂ!!

ሌንሣ -/በበለጠ ትእዝብት አዘል ቅዛዜ ልሣን/- አዘጋጅ ቢ.አራጋው። ካንተ ጋር መኖር ያስቻለኝን አምላክ አመሰግን።.....እንኳን ደስ አለህ ኧ! ምሥጋና ቢሱ።....አዶዬ ግደይና እኔ፣ አስተራርቀናችኋል።

ቢ.አራጋው አፋ!! -/ጋሪውን መንጭቆ ግማሽ መድረክ ላይ ትቶ ተፈናጥሮ ሊወጣ ሲል ድንገት ይቆማል። ፉት ሮጣ ገብታ ሌንሣ ጉን ስትቆም በታላቅ ቁጣ እንባርቆ ይጠራታል/-

ዳንኪረኛ ፉት! ዳንኪረኛ ፉት! ነይ! -/ፈርታ ተንቀጥቅጣ ትቀርበዋለች። ያንባርታል/-ምን ሊያጥደፈድፍ ምን ሊያክነፈንፍ አመጣሽ አንቺን ደሞ?!

ፉት -/እየተንቀጠቀጠች/- ዳንኪረኛ ሌንሣና ዳንኪረኛ ግደይ ከወንድምህ ጋር አስተራርቀዋችኋል ልልህ ብቻ ነው አዘጋጅ ቢ--

ቢ.አራጋው -/እንባርቆ ያጽርጣታል/- አንቺን ምን ያገባሻል?!-/ዛቻ/- ቆይ አንቺን ደሞ ገና ልክ ባላስረግጥሽ! ልክ ባላስደንስሽ! እኔ ቢ.አራጋጋው አረጋው! -/ተፈናጥሮ ይወጣል። ግደይ ትገባለች/-

እስተራርቀናቸዋል–/ ዘፈን ደንኪራ በሲዳማ ባህልና እስቴር አወቃቂ ዓይነት ሰልት እየደነከሩ በዳንኪረኛ ግደይ መሪነት በህብረት ይዘፍናሉ። /–

እስተራራቅኔካ፣ አ

እፋቃቃርኔካ፣ አ

እቃራራብኔካ፣ አ

እከባባርኔካ፣ አ

እፋቃቃድኔካ፣ አ

እስተራርቀናቸዋል፣ አ

አፈቃቀድናቸዋል፣ አ

እስታርቀናቸዋል ተመስገን ላይሉ
መጥኔ ወንድማማች ምሥጋና ቢስ ሁሉ

ኩኩሉሉ ሉሉ፣ ኩኩሉሉ ሉሉ

እስታርቀናችኋል ተመስገን ላትሉ

መጥኔ ወንድማማች ምሥጋና ቢስ ሁሉ

አዘጋጅ ቢ. አራጋው ነጋ ኩኩ ሉሉ

ኩኩሉሉ ሉሉ፣ ኩኩ፣ ሉሉ፣ ሉሉ

–/መብራት ይጠፋል። መብራት የበራል። ትዕይንት አቋም ሁለት የቀጥላል።/–

ደብዛዝ መብራት ይበራባቸዋል። ዳንኪረኛ ገደይ የወንዲውን አዝማች እየተንጉራደደች ትዋ ነያለች/-

/አረሆዎች/ አዝማች:-ንገራችው ለቡሽ እባክህን ኮሽን

በእንደበትህ መገን

ከቻልክ አስተራርቀን

ካታተህም ተወን

በምላስህ ብዛት ጭረህ አታሟርሰን

ከምድር አታስጠፋን፣ ወገንን በወገን

ኮሽን ተለመነን

እባክህን ኮሽን

ተወን-ተወን-ተወን!

-/እሩምታ ተኩስ ከመድረክ ጀርባ ሲያስተጋባ አረሆዎች እርጭ ይላሉ። መብራት ከእሩምታ ተኩሱ ጋር ይጠፋል። ነጥብ መብራት መድረክ ግንባር ይበራል። ነጋ ከሕዝብ መሀል ተንደርድሮ ግንባር መድረክ መብራት መሀል ይቆማል። ሁለቱን ሕፃናትና ፊደል ገበታዎች አዝሏል። ትእይንት ፊደል ጉዞ ይቀጥላል።/-



ሥሬት ፀጋቱ ከሠሙ ወይም ፕፑ ተዋንያን ጋር



ምነው?! -/ፋታ/-

እናቶች፣ አባቶች

እህቶች፣ ወንድሞች

ተበላን በምሁር ጅቦች!

የልባችን ቋት ዉለመ።

ብልጥታው ተረመረመ።

ምነው?! -/ፋታ/-

በአንድ ጅራፍ ለተገረፍን፣

በአንድ እርግማን ለተኮነን፣

እኛው ነን የኛ መድኃኒት

ከኛ እንጂ ከውጪ አይመጣም፣ የነገ ተስፋችን መክሊት።
-/ረጅም ፋታ። ቆራጥ ቀዛዝ ልሣን/-

እሄዳለሁ። ያባቴን ቃል ተሸክሜ

እስከ ዕድሜ አዚሜ ፍፃሜ

ሕዝቦቼ መሀል ገብቼ፣ ያገሬን ድንበር ዞራለሁ

የእናቴን ልጆች አልፈራም። እሄዳለሁ።.....

እስከዛሬ ብዙ ፈራን!

ፍርሃት በቃን!

ምነው?!
-/ከመድረክ ጀርባ እሩምታ ይተኮሳል። ነጋ እየተንደረደረ ተኩሱ ወደ ተሰማበት አቅጣጫ ይገሰግሳል/-

-/መድረክ ጭስባር ቆሞ ትጥቁንና ገመዱን ፈትቶ ወደ መሬት ይወረውራል። ይገሰግሳል። ሀ ሁ ሂ ሃ ሄ ህ ሆ ሰላም ሲከዌል ሙዚቃ ግሥጋሤውን ከሩቅ እያጀበው መብራት ይጠፋል። ተዋንያን በጭለማው ውስጥ በሲከዌል ታጅበው እያዜሙ እጅ ይነሳሉ።/-

መዝሊያ-ሲከዌል:-ህ ሁ ሂ ሃ ሄ ህ ሆ
ወይስ ጦር ፐ ፑ ፓ ፖ!
አቡጊዳ ቀይሶ
ወይም ሰላም ፈልሶ
ሚሊዮን ሰው ገንዞ!?....
መልእክተ ሳብ አደር
ወይም የአሥራ ሰባት ጠር!?....
ሰላም ፍትህ እብቦ
ዴሞክራሲ ወሽቦ
ሰላም ሀሁሂሃሆ
ወይም ጦር ፐፑፓፖ!

-/ተፈጸመ/-

